ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 033 ጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ፍትሃዊነትን የማስፈን ትብብር


ፋንታነሽ ክንዴ


**ዜና ትንታኔ**

ከ11 የናይል ተፋሰስ ሀገራት መካከል ስድስቱ የተፋሰሱን የትብብር ማዕቀፍ አጽድቀዋል፡፡ ይህም የናይል ተፋሰስ ኮሚሽንን ለማቋቋምና በዓባይ ወንዝ ዙሪያ የሚስተዋሉ ኢፍትሃዊነትና አለመግባባቶችን በማስቀረት ትብብርን መሠረት ያደረገ የጋራ ተጠቃሚነትን እንደሚፈጥር የዘርፉ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለመሆኑ የናይል ተፋሰስ ትብብር ማዕቀፍ ለተፋሱ ሀገራት የሚኖረው ፋይዳ ምንድነው? ፍትሃዊነትን ከማስፈን አንጻር የሚያበረክተው አስተዋጽኦስ ምን ይመስላል?

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ እንደሚሉት፤ የናይል ተፋሰስ 11 ሀገሮችን ያካትታል፡፡ ከዚህ ውስጥ ዘጠኙ የተፋሰሱን ማዕቀፍ ለማቋቋም እና በተፋሰሱ ስር ያሉትን የትብብር ሥርዓቶች


ፍትሐዊነትን የማስፈን ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል


# ሰንደቃችን በሰንደቅ አርበኞች


ዮርዳኖስ ፍቅሩ


ሰንደቅ ዓላማ የአንድ ሕዝብ ምልክት ነው፡፡ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የኩራት፣ የጥንካሬ፣ የአይበገሬነት መገለጫም ነው፡፡ ኢትዮጵያ በየዘመናቱ ሉዓላዊነትን ባስከበሩ ፍልሚያዎችና በሠላማዊ የትግል ሜዳ ሰንደቋን ከፍ ያደረጉ ጀግኖችን አፍርታለች፡፡ ጀግናው መከላከያችን ሀገራችንን ወራሪ ጠላትን ድል አድርጎ ሰንደቃችንን ሲያውለበልብ ልቡ በሐሴት የማይሞቅ፣ ጀግኖች አትሌቶቻችንም በሠላማዊው የስፖርት ትግል መድረክ ድልን ተቀዳጅተው ሰንደቃችንን ሲያነሱ የደስታ ሳግ የማይተናነቀው ኢትዮጵያዊ አይኖርም፡፡

ረዳት ኮሚሽነር ማርቆስ ገነቴ፣ ወታደርና አትሌት ለሰንደቅ ዓላማ ጠንካራ ስሜትና የጠበቀ ቁርኝት እንዳለቸው ይናገራል፡፡ “ከአትሌትነቱም በተጨማሪ ውትድርና ሙያዬ በመሆኑ ለሰንደቅ ዓላማችን ያለኝ ስሜት ጥልቅና የተለየ ነው” ይላል፡፡




በሁለቱም ሙያ የሀገሩን ሰንደቅ ለማስጠበቅ የቆመው ረዳት ኮሚሽነር ማርቆስ በአትሌቲክሱ መስክ ከጀግናው አበበ ቢቂላ ጀምሮ አትሌት ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ቀነኒሳ በቀለ እና የአሁን ዘመን የኦሎምፒክ ጀግኖች አትሌት ታምራት ቶላ እና ትዕግስት አሰፋን ጨምሮ ሌሎችም በርካቶች በልፋት፣ በብዙ ጥረትና በሀገር ፍቅር ስሜት በዓለም አደባባዮች ላይ የሀገራቸው ሰንደቅ ከሌሎች ሀገራት ሰንደቆች ይልቅ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ያስቻሉ የኢትዮጵያ ጀግኖች መሆናቸውን አንስቷል፡፡

አትሌቱ እንደገለፀው፣ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በባዕድ ሀገር ሀገራቸውን ወክለው ለድል ሲታገሉ በየጎዳናው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው የሀገራቸውን ልጆች የሚያበረቱ ኢትዮጵያውያንን መመልከት ጥልቅ ስሜትን የሚፈጥር ነው፡፡

በውድድር ላይ እያለን በሌሎች ሕዝቦች ምድር ላይ ኢትዮጵያውያንን እና ሰንደቃችንን መመልከት ትልቅ ብርታት የሚሰጥ ስንቅ ነው ያለው ኮሚሽነር ማርቆስ፣ ድል አድርገን ሰንደቃችን ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ማድረግ የሚሰጠው ስሜት ደግሞ በቃላት መግለጽ የሚቻል አይደለም፡፡ ጥልቅ ስሜትን ይፈጥራል ሲል ይናገራል፡፡

አትሌቱ ሀገሩን ወክሎ በዓለም የስፖርት ውድድር


ሰንደቃችን ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል


# የአእምሮ ህመምና ህክምናው


መስከረም ሰይፉ


**ዜና ሀተታ**

የሥነ አእምሮ ሳይንስ በዓለም በተለይም በአፍሪካ ገና በማቆጥቆጥ ላይ እንዳለ በሥነ አእምሮ ህክምና ዙሪያ የተጻፉ የተለያዩ


የአእምሮ ህመምና ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

















ዜና

# የቫይታሚን ዲ እጥረትና መፍትሄው

**ማህሌት ብዙነህ**

**ዜና ሀተታ**

ቫይታሚን ዲ ከ5ቱ የቫይታሚን አይነቶች ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን በዋነኝነት ሰውነታችን ካልሲየም እና ፎስፎረስ የተባሉትን ንጥረነገሮችን በደም አማካኝነት ከአንጀት ክፍል ወደ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻችን እንዲዳረሱ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው:: በተጨማሪም የበሽታ የመከላከል እና የመቋቋም አቅማችንን የሚጨምርና ለህዋሳት እድገት አስፈላጊ የሆነ የቫይታሚን አይነት እንደሆነ የጤና ባለሙያዎች ይገልጻሉ::

በዚህም ጨቅላዎች በቀን 400 አለምአቀፍ የቫይታሚን ዲ ዩኒት (IU) ልጆችና ጎልማሶች ደግሞ በቀኑ ከ600 ዓለምአቀፍ የቫይታሚን ዲ ዩኒት (IU) ማግኘት አለባቸው ይላሉ:: እድሜያቸው ከ 70 በላይ ዓመት የሆናቸው ሰዎች እስከ 800 ዓለምአቀፍ የቫይታሚን ዲ ዩኒት (IU)ማግኘት እንዳለባቸው ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

ታዲያ በሰውነት ውስጥ በቂ የሆነ የቫይታሚን ዲ ክምችት አለመኖር የቫይታሚን ዲ እጥረት የሚያስከትል ሲሆን ይህም ሕጻናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንቶችን ጨምሮ ማንኛውምን የሕብረተሰብ ክፍል ሊያጠቃ ይችላል:: በዓለም ዙሪያም ከ 8 ሰዎች መካከል አንዱ የቫይታሚን ዲ እጥረት አለባቸው ተብሎም እንደሚገመት መረጃዎች ያሣያሉ::

የቫይታሚን ዲ እጥረት ምንነት፣ መከላከያ መንገዶችና ስለሚያስከትለው የጤና ዕክል ኢፕድ የጤና ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ሞገስ አብርሃን አነጋግሯል

ዶክተር ሞገስ እንደገለጹትም፤ ቫይታሚን ዲ ለአጥንት ጥንካሬ፣ ለደም እና በአጥንት ውስጥ የካልሲየም ሚዛን ለመጠበቅ ፣ ለጤናማ ጡንቻዎች ብሎም እንደ ስኳርና ልብ የመሳሰሉ በሽታዎች መከላከያ ሥርዓቶችን ለመደገፍ የሚያስችል ለሰውነት አስፈላጊ የሆነ ንጥረ ነገር ነው::

በመሆኑም አንድ ሰው በቀን ከ600 እስከ 800 ዓለምአቀፍ የቫይታሚን ዲ ዩኒት (IU)ማግኘት አለበት:: በተለይም እድሜያቸው ከ45 ዓመት በላይ የሆኑ ሴቶች በቀላሉ ለስብራት የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የቫይታሚን ዲ በሚያስፈልገው ልክ መውሰድ አለባቸው ይላሉ::



በቂ ያልሆነ የቫይታሚን ዲ ያላካተተ አመጋገብ እና በቂ የፀሀይ ብርሃን አለማግኘት በዋነኝነት ለቫይታሚን ዲ ለእጥረት የሚያጋልጡ ነው:: ይህም በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ሊከሰት የሚችል መሆኑን አስታውቀዋል::

ቫይታሚን ዲ በሰውነታቸውን ውስጥ በበቂ መጠን አለመኖር ለአጥንት መሳሳት፣ ጡንቻ ህመም፣ የሰውነት መተሳሰር እና የድካም ስሜት፣ እንደ ድብርት ያሉ የስሜት ለውጦችን እንዲሁም የበሽታ የመቋቋም አቅማችንን እንዲቀንስና ቶሎ ቶሎ በበሽታ የመጠቃት እድልን የሚጨምር መሆኑንን ገልጸዋል::

ቫይታሚን ዲ ከጸሀይ ብርሃን እንዲሁም እንደ ወተት፣ የዓሳ ዘይት፣ እንቁላል፣ እንደብርቱካን፣ ሙዝ እና አቮካዶ ያሉ የአትክልት ውጤቶች ፣ እርጎ፣ ዓሳ ያሉ ብዙ ቫይታሚን ዲ ያላቸው ምግቦች እና መጠጦች ማግኘት የሚቻል መሆኑንም ይገልጻሉ::

ዶክተር ሞገስ እንደሚሉት ፤ ሰውነታችን ቆዳ ላይ የሚያርፈውን የፀሐይ ብርሃን በመጠቀም 7 ዳይሀድሮኮሌስትሮል የተባለውን በተፈጥሮ በቆዳችን ውስጥ የሚገኘውን ውህድ ወደ ቅድመ ቫይታሚን ዲ3 በመቀየር ሰውነታችን ቫይታሚን ዲን ከፀሀይ ማግኘት ይችላል::

ምንም እንኳን የጸሀይ ብርሃን በሰውነታችን ውስጥ ቫይታሚን ዲ እንዲመረት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ቢሆንም አብዛኛው ሰው የጸሀይ መሞቅ ልማድ ዝቅተኛ መሆኑን አንስተው፤ በዚህም ከፍተኛ በቫይታሚን ዲ እጥረት የመጋለጥ እድል እንዳላቸው ይገልጻሉ::

በሳምንት ቢያንስ ሶስት ቀን ለ20 ደቂቃ ጸሀይ በመሞቅ በቂ ቫይታሚን ዲ ማግኘትትና በቫይታሚን ዲ እጥረት የሚከሰቱ የጤና ዕክሎችን መከላከል እንደሚገባም ተናግረዋል::

በቂ ቫይታሚን ዲ ከምግባቸው ወይም ከጸሀይ ያላገኙ ሰዎች በየቀኑ ከ600 እስከ 800 IU (ዓለምአቀፍ የቫይታሚን ዲ ዩኒት) ያላቸውን ማሟያ እንክብሎች ወይም ፈሳሾች (የቫይታሚን ዲ ሰፕልመንት) የህክምና ባለሙያዎችን ጋር በመሄድ መጠቀም የሚችሉ መሆኑን ገልጸዋል::

የተጠቀሱት ምልክቶች በራሱ ላይ ያስተዋለ ሰው እንዲሁም በአቅራቢያው ያለ የህክምና ተቋም በመሄድ የቫይታሚን ዲ መጠንን የደም ምርመራ በማድረግ ማወቅ የሚቻል ሲሆን የመከላከያ መንገዶቹን በመጠቀም ሁሉም ዜጋ ጤናውን መጠበቅ ይገባል ሲሉ መክረዋል::

# በዞኑ በዘንድሮ የትምህርት ዘመን ከ197 ሺህ በላይ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች ተሰራጭተዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዲላ፡- በጌዴኦ ዞን በዘንድሮ የትምህርት ዘመን ከ197 ሺህ በላይ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች መሰራጨታቸውን የዞኑ ትምህርት መምሪያ አስታወቀ።

የጌዴኦ ዞን ትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘማች ክፍሌ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዞኑ የመማሪያ መጽሐፍ ችግሮችን ለመፍታት ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጽሐፍ በክልልና በዞን የጋራ ትብብር የሚታተም ነው።

ለዚህም እንደጌዲዮ ዞን አንድ መጽሐፍ ለአንድ ተማሪ በሚል እንቅስቃሴ ከ22 ሚሊዮን ብር በላይ ማሰባሰብ ተችሏል። በዚህም የመማሪያ መጽሐፍት እየታተሙ ይገኛል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማሪያ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር የሚታተም ሲሆን ይህንንም በፍጥነት የማሰራጨት ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

በዞኑ በዘንድሮ የትምህርት ዘመን ከ197 ሺህ በላይ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎች ተሠራጭተዋል ያሉት አቶ ዘማች፤ በዘንድሮ ዓመት ከ197 ሺህ በላይ መማሪያና ማስተማሪያ መጽሐፎችን ከክልል ትምህርት ቢሮና ከትምህርት ሚኒስቴር ተረክበን ማሰራጨት ችለናል ። በዚህም ከአራተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ መጽሐፎች ተሰራጭተዋል ነው ያሉት።

ከቅድመ አንደኛ እስከ ሶስተኛ ክፍል ያሉ መጽሐፎች ወደ ማተሚያ ቤት ለህትመት እንደገቡ የገለጹት አቶ ዘማች፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጽሐፍ መሰራጨቱንም ገልጸዋል። ዘንድሮ በሁሉም የትምህርት እርከኖች ከአንድ ለአንድ እስከ አንድ ለአምስት መጽሐፎች በሁሉም የትምህርት አይነት ለማዳረስ የሚያስችል ሥርዓት መፈጠሩን ተናግረዋል።

በዚህ ደረጃ የትምህርት ቤቶች ትልቅ ተግዳሮት የሆነውን የመጽሐፍ እጥረት ከሞላ ጎደል እየተፈታ ነው ያሉት አቶ ዘማች፤ እንደዞን የግብዓት አቅርቦት ለትምህርት ስኬት በሚል መሪ ሃሳብ ሁሉም ትምህርት ቤት ወጥ በመሆነ መንገድ ያላቸውን መጽሐፍ ለተማሪዎች እንዲያስተላልፉ ተደርጓል ብለዋል።

አሁን ላይ በዞኑ የመጽሐፍ ማከማቻ ቦታ ላይ የተቀመጠ መጽሐፍ አለመኖሩን ተናግረው፤ አሁን ላይ የታተሙ መጽሐፎች በእጃችን አለመኖሩን እና ከትምህርት ሚኒስቴርና ከክልል ትምህርት ቢሮ በኩል ታትመው የሚሰጡንን መጽሐፎች በፍጥነት ለማዳረስ መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በዞኑ 327 ትምህርት ቤቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ አምና ወደ 295 ሺህ መጽሐፎችን ለትምህርት ቤቶች ማዳረስ ተችሏል ብለዋል። የትምህርት ሥርዓቱ በቅርቡ የተሻሻለ መሆኑ፣ የኢኮኖሚያዊ አቅም ዝቅተኛ መሆን የመጽሐፍ ተደራሽነት ላይ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አንስተዋል።

# ኮሌጁ በድህረ ምረቃ ያሠለጠናቸውን 410 ተማሪዎች አስመረቀ

**ሞገስ ጸጋየ**

አዲስ አበባ፡- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ በድህረ ምረቃ ያሠለጠናቸውን 410 ተማሪዎችን አስመረቀ።

በምረቃ ሥነሥርዓቱ ላይ የእንኳን ደስ አላችሁ ንግግር ያደረጉት የኮሌጁ ፕሮቮስት ዶክተር ሲሳይ ስርጉ እንዳሉት፤ ኮሌጁ ለ11 ጊዜ የምረቃ ሥነሥርዓት አካሂዷል። ሁሉም ተመራቂዎችም የድህረት ምረቃ ተማሪዎች ናቸው። ከህክምና ትምህርት ቤት ሶስት መቶ ተመራቂዎች፣ ሁለት መቶ ሃያ በስፔሻሊቲ ሥልጠና፣ 36 ተማሪዎች በ11 ሰብ ስፔሻሊስት ስልጠና፣ 14 ተማሪዎች በሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ሥልጠና መስከ ሠልጥነው መመረቅ ችለዋል።

እንዲሁም ከህብረተሰብ ትምህርት ቤት 58 ተመራቂዎች በአራት የትምህርት ዘርፎች ተመርቀዋል። እንዲሁም ከነርሲንግ ትምህርት ክፍል 52 ተመራቂዎች በስድስት የትምህርት መስከ የተመረቁ ሲሆን በአጠቃላይ 410 ተመራቂዎች በ43 የተለያዩ የትምህርት መስኮች መመረቃቸውን ጠቅሰዋል።



እንደ ዶክተር ሲሳይ ገለጻ፣ የተመራቂዎች የትምህርት መስከ ስብጥር እንደሚያሳየው የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም ህክምና ኮሌጅ ጤና ሚኒስቴር ያወጣውን ስፔሻሊቲና ሰብ ስፔሳሊቲ ፍኖተ ካርታ መሠረት ያደረገ ሥልጠና ነው። ይህም የህክምና ዘርፉን ለማዘመን፣ ለማሳደግ፣ ጥራቱ የጠበቀና ተደራሽ ለማድረግ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ትልቅ መሆኑን ገልጸዋል።

ተመራቂ ተማሪዎች በኮሌጁ ስር በሚገኙ ሆስፒታሎችና ከኮሌጁ ጋር በጋራ በሚሠሩ ሆስፒታሎች ላይ የተግባር ልምምድ አድርገዋል። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ ወረርሽኞችን የቅኝትና ምላሽ መስጠት ላይ በመሳተፍ የተግባር ልምድ እንዲያገኙ መደረጉን አመልክተዋል።

ተመራቂ ተማሪዎች ወደ ሥራ ሲሰማሩ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ይችላሉ ያሉት ዶክተር ሲሳይ፣ በተደረጉ የማህበረሰብ አገልግሎቶች በመሳተፍ ትልቅ ሥራ ሠርተዋል። እንዲሁም በሀገሪቱ በተከሰቱ ሰው ሠራሽ ችግሮች፣ ድንገተኛ አደጋዎችና የወረርሽኝ ምላሽ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን በመግለጽ፣ ምስጋና አቅርበዋል።

እንደ ፕሮቮስት ዶክተር ሲሳይ ማብራሪያ፣ ኮሌጁ የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ ለማስፋፋት ባደረገው ጥረት በአሁኑ ጊዜ በ73 የቅድመ መደበኛና የድህረ ምረቅት ሥልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል። የትምህርት መስኮችን ከማስፋፋት በተጨማሪ የሥልጠናዎች ተግባር ተኮር ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል።

አዳዲስ የህክምና አገልግሎቶችን ለማስፋፋት፣ የነበሩትን ደረጃቸውንና ጥራታቸውን በማሻሻል በተለይም የነርሲንግ ሥልጠናዎችን ወደ ሪዚደንሲ የሥልጠና ስልት በመቀየር ውጤታማ ሥራ መሥራቱን ተናግረዋል ።

የክህምና ትምህርት ቤትን ዓለም አቀፍ እውቅና ለማሰጠት የሚያስችል ማመልከቻ ለማስገባት የመጨረሻ ዝግጅቱ ተጠናቋል። ግንባታቸው ተጠናቆ በቅርቡ ወደ አገልግሎት ለመግባት በዝግጅት ላይ የሚገኙት የካንሰር ፣ የልብ፣ የአንጀትና የጉበት የህክምና ማእከሎች ከሚሰጡት ከፍ ያለ አገልግሎት እንዲሰጡ ብቁ ባለሙያዎችን የማብቃት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ዶክተር ሲሳይ ጠቁመዋል።

# ሰንደቃችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተሳተፈባቸውና ድልን ከተቀዳጀባቸው በርካታ የውድድር መድረኮች ሁሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀንጋሪ የዓለም ወጣቶች ሻንፒዮን ላይ ወርቅ አምጥቶ የሀገሩ ሰንደቅ ከፍ እንዲልና ብሔራዊ መዝሙራችንም እንዲዘመር ያደረገበትን ክስተት በሕይወቱ ከተቀዳጃቸው ድሎች ሁሉ ቀዳሚውን ሥፍራ የሚሰጠው እንደሆነም ተናግሯል::

“ኢትዮጵያ” ከጥንት ጀምሮ ቅድመ አያቶቻችን፣ አባቶቻችን ለሰንደቃቸው ተጋድለው ያስተላለፉልን ሀገር ናት ያለው ኮሚሽነር ማርቆስ፣ ይህችን ጥንታዊትና ታሪካዊ ሀገር ከነክብሯ የማስረከብ አደራና ኃላፊነት አለብን ብሏል። በተለይም ወጣቱ ትውልድ ይህን ተገንዝቦ ይህችን በዓለም መድረክ ብዙ የሚያኮራና የሚደነቅ ገጽታዎች ያሏትን ሀገር በየተሰማራበት መስከ ሁሉ በሀገርና በሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ስሜት ማገልገል እንደሚገባው ይመክራል::

ነገ “ሰንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ከፍታ” በሚል መሪ ሃሳብ ለ17 ጊዜ በመላው ሀገራችን ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ይከበራል:: ቀኑን አስመልክቶም “እንደ ጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን፣ እንደ ጀግኖች አትሌቶቻችን ለሰንደቃቸው ዋጋ እየከፈሉ እንዳሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በየተሰማራንበት ሙያ ለሀገራችን ክብርና ከፍታ የምንችለውን ሁሉ መስዋእትነት ለመክፈል እየተጋን ይሁን ሲል መልዕክቱን ያስተላልፋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕይወትን ለመስዋእት ከማዘጋጀት በፊት

የትግራይ ሕዝብ እንደ ሕዝብ በዘመናት መካከል በኢትዮጵያዊነቱ ተደራድሮ የማያውቅ ፣ በሀገረ መንግሥት ግንባታውም ሆነ ፤ ሀገረ መንግሥቱን አጽንቶ በማስቀጠል ሂደት ውስጥ ሰፊ አበርክቶ ያለው ሕዝብ ነው ። በታሪክ የኢትዮጵያውያንን እጣ ፈንታ የተጋራ ወደፊትም ቢሆን እጣፈንታው ከኢትዮጵያዊ ወንድሞቹ ጋር የሚጋራ ሕዝብ ነው።

እንደ ሀገር የትናንት ታሪካችን ደማቅ አካል የሆነው የትግራይ ሕዝብ ፤ ከፍ ባለ ሃይማኖታዊ እና ማኅበረሰባዊ ሥነምግባር የሚጠቀስ ፤ እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለፍትህ እና ለነጻነት ቀናኢ የሆነ ፤ ለብሔራዊ ክብር ራሱን መስዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ሁሌም ዝግጁ የሆነ ፤ ለፍቅር እና ከዚህ ለሚመነጭ ወንድማማችነት ትልቅ ቦታ የሚሰጥ ሕዝብ ነው።

ከሳለፉቸው ብዙ የሰላም እጦት ዓመታት ፤ በነዚህ ዓመታት ከከፈላቸው ተዘርዝረው የማያልቁ አላስፈላጊ ዋጋዎች አኳያ ፤ ሰላም እና ከሰላም የሚመነጭ ሕይወትን ለራሱ ፣ ለሀገሩ እና ለመጪዎቹ ትውልዶች አብዝቶ የሚመኝ ፤ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት ያለው ሕዝብ ነው ።

ይህ ሕዝብ ማኅበረሰባዊ ማንነቱ ከተገነባበት መንፈሳዊ እና ማህበረሰባዊ እሴቶቹ፤ ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ከተጓዘባቸው የሕይወት ውጣ ውረዶች ካካበተው ተጨባጭ ተሞክሮ አኳያ፤ ከጦርነት እና ከግጭት ተጠቃሚ የሚያደርገው ምንም ነገር ሊኖር እንደማይችል በአግባቡ የተረዳ ነው ።

ይህንን ሕዝብ እናውቀዋለን እንወክለዋለን ፤ የሚሉ ፖለቲከኞች ከሁሉም በፊት ይህንን የሕዝቡን አሁናዊ እውነታ በአግባቡ ሊረዱ ፤ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያቸው ከዚህ የማኅበረሰብ ተጨባጭ እውነታ ጋር የተጣጠመ መሆኑን ቆም ብለው በሰከነ መንፈስ ሊያስቡት ይገባል።

ይህ ሕዝብ ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት በነጻነት፣ በዴሞክራሲ እና በፍትህ ስም በተካሄደው መራራ ትግል ምን ያህል የትግሉ ተጠቃሚ ነበርኩ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከማንም በላይ ሊናገር የሚችለው ራሱ ነው። በትግሉ ወቅት የከፈለው መስዋእትነት ምን ያህል የነጻነት፣ የዴሞክራሲ እና የፍትህ ጥማቱን አርክቶታል ለሚለውም መልሱ በእጁ ነው።

ከዚህም ባለፈ ከለውጡ ማግስት በፌዴራል መንግሥቱ እና በሕወሓት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት በተቀሰቀሰው ጦርነት የቱን ያህል ዋጋ እንደከፈለ ፣ ምን ያህል ልብ ሰባሪ በሆነ ክስተት ውስጥ እንዳለፈ ፤ ክስተቱ ምን ያህል ሕዝቡን ተጨማሪ የኀዘን ማቅ እንዳለበሰው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የትግራይ ሕዝብ በነጻነት፣ በዴሞክራሲ እና በፍትህ ስም ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት ብዙ መስዋዕትነት ከፍሎ ፍላጎቶቹን ተጨባጭ ማድረግ አልቻለም ፣ ለምን ለተመሳሳይ የዓላማ ትርክት በየጊዜው መስዋእት ለመክፈል ይገደዳል ፤ መስዋእትነቱ ፍሬ ላለማፍራቱስ ማነው ተጠያቂ የሚሉትን ጥያቄዎች አሁን ላይ ማንሳት ተገቢ ነው።

ሀገርን ጨምሮ የትግራይ እናቶች በብዙ ተስፋ የሚጠብቋቸው የትግራይ ወጣቶች በየወቅቱ በሚፈጠር አለመግባባት ለሞት እና ለስደት የሚዳረጉበት እውነታ ማብቂያው መቼ ነው?፣ ለትናንቱም ሆነ ለዛሬው ጥፋት ተጠያቂ ማነው ፣ ጥያቄው አሁን ላይ ምላሽ የሚፈልግ ፤ የትግራይን ሕዝብ ወደሚፈልገው ሰላም እና መረጋጋት የሚያመጣ ነው።

የትግራይ ሕዝብ እንደ አንድ ትልቅ የታሪክ ባለቤት ሕዝብ ምንድነው እየሆነ ያለው በሚል ቆም ብሎ ሊያስብ ወደሚያስችለው ስክነት ሊመጣ ይገባል ፣ አላስፈላጊ ዋጋ እየከፈለ ካለበት የግጭት አዙሪት ወጥቶ የራሱን ዕጣ ፈንታ በራሱ ወደሚወስንበት የታሪክ ምዕራፍ ሊሸጋገርም ይገባል ።

በተለይም ወጣቱ ትውልድ ካለበት ነባራዊ እውነታ አኳያ የራሱን እና የክልሉን ሕዝብ ዕጣ ፈንታ መወሰን በሚያስችል ዝግጁነት ራሱን ማብቃት፣ ትናንት ለነጻነት፣ ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ሕይወታቸውን የገበሩ ሰማዕታት መስዋእትነት በተጨባጭ ለትግራይ ሕዝብ ምን አተረፈለት ፣ ዛሬስ ያለው እውነታ ምን ያተርፍለታል የሚለውን በአግባቡ ሊመረምር ይገባል።

የጦርነት ከበሮ በተጎሰመ ቁጥር ፣ ሕይወቱን ለመሰዋዕት ከማዘጋጀት በፊት መስዋዕትነቱ በተጨባጭ ለትግራይ ሕዝብ ምን አዲስ ነገር ይዞ ይመጣል ፣ የተነስ ታጠቅ ጥሪ ከትናንት እንደ ሕዝብ ብዙ መስዋእትነት ካስከፈለው ተመሳሳይ ጥሪ በምን ይለያል ለሚለው ጥያቄም በቅድሚያ ምላሽ ሊያገኝለት ይገባል።

እንደ ትውልድ ካለው የራሱ መሻት/መፈለግ አንጻር ፤ በክልሉ ትናንት ሆነ ዛሬ የሆነው እና እየሆነ ያለው እውነታ ምን ትርጉም አለው? ፤ በሱ እጣ ፈንታ ላይ እየወሰነ ያለው ፤ ለምን እንዲወስን ሆነ ፤ አቅም ስለሌለው ወይስ አማራጭ ስለተነፈገ ? የሚለውንም ጉዳይ በአግባቡ ሊመረምረው ይገባል ።

እንደ ትውልድ ፍላጎቱ ምንድነው ? የጦርነት ገድል ወይስ ሰላም እና ከሰላም የሚመነጭ ልማት ፤ ወደ ግጭት የሚወስድ የጥላቻ ትርክት ወይስ በአብሮነት ትርክት የተሻሉ ነገዎችን መፍጠር ወደሚያስችል አዲስ የታሪክ ጅማሬ መምጣት የሚለውንም ጉዳይ አጥርቶ መመለስ ይጠበቅበታል ። ይህን ማድረግ ሲችልም ለራሱም ሆነ ለመጪው ትውልድ መትረፍ ይችላል!


**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የወደብ ጥያቄ ካልተገባ ሆሆይታ ወጥቶ በስክነት እና በወዳጅነት ማጤን ተገቢ ነው

ዮናታን ጠለለው ብዙነህ

ለወትሮውም ከጥይት ድምፅ ነፃ ሆኖ ያልከረመው የአፍሪካ ቀንድ ቀጣና በይዘቱ ከፍ ያለ ጦርነት በቅርቡ የተደገሰለት ይመስላል፡፡ ቀይ ባህርን ዋነኛ መነሻው ያደረገ የሚመስለው ይህ አለመረጋጋት፣ ከሰሞኑን ደግሞ የእጅ አዙር ጦርነት /Proxy War/ የማካሄድ እቅድ ባላቸው እንደ ግብፅ ባሉ ሀገራት እንቅስቃሴ ውጥረቱ ከፍ ብሏል፡፡

በ 2050 ዓ.ም 1.32 ቢሊዮን ገደማ ሕዝቦች መኖሪያ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው የቀይ ባህር ዙሪያ የመላው ዓለም የዓይን ማረፊያ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጧል። ከጥቂት አስርት ዓመታት በፊት የባህር በር የነበራት ኢትዮጵያም በታሪክ አጋጣሚ ባጣችው መተንፈሻ ምክንያት በአካባቢው የነበራት ተፅእኖ ተቀዛቅዞ ቆይቷል።

ይህን ተከትሎ የመጡ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችም ሀገሪቷን ብዙ ዋጋ እያስከፈሏት ነው። ከመረጋጋት በራቀው እና እንደ አልሸባብ ላሉ ሽብርተኛ ቡድኖች መነሃሪያ በሆነው የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና እንደመገኘቷ፣ ከባህር የሚቃጡ ስጋቶችን ለመከላከል ሆነ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የሕዝብ ቁጥሯን ተሳቢ ያደረገ እድገት ለማስመዝገብ የባህር በር ያስፈልጋታል። ይህን ታሳቢ በማድረግም እንቅስቃሴዎችን ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡

ይህንን እንቅስቃሴ ወደ ፍሬ ለማብቃት መንግሥት በአካባቢው ለሚገኙ የወደብ ባለቤት ሀገራት ጥሪ አቅርቧል ፤ ጥሪውን ተከትሎም የሶማሌ ላንድ መንግሥት ምላሽ ሰጥቷል ። ምላሹን ተከትሎም የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል። በዚህም በአካባቢው ብሄራዊ ጥቅም አለን የሚሉ ሃይሎች አካባቢውን ወደ ግጭት ለመውሰድ ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ።

ስለ ቀይ ባህር እና ስለ ወደብ፣ ማውራት እንደ ነውር የሚታይባቸውን 27 ዓመታት ተሻግረን አሁን ላይ ፤ አጀንዳውን ሀገራዊ ከዛም ባለፈ ዓለም አቀፋዊ የማድረጉ እውነታ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ድጋፍ አግኝቷል። ጥያቄው ከሕግ እና ከሞራል አኳያ ትክክል ስለመሆኑም በብዙዎች ዘንድ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ ነው፡፡ ዓለም አቀፍ እውቅናም እያገኘ ነው።

ይህም ሆኖ ግን በአካባቢው ብሄራዊ ጥቅም አለኝ የምትለው ግብጽ ፤ ከጉዳዩ ባለቤቶች በላይ ለጉዳዩ ባለቤት በመሆን ፤ የወደብ ጥያቄውን የዓባይ ውሃ ቀጣይ አጀንዳ በማድረግ፤ አካባቢውን ለማመስ በተለመደው መንገድ መንቀሳቀስ ከጀመረች ውላ አድራለች ።

ጉዳዩን አስመልክቶ አልጀዚራ ባለፈው ወር የግብፅን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መግለጫን እማኝ በማድረግ ይዞት በወጣው ዘገባ ፤ ግብፅ ከአራት አስርት ዓመታት በኋላ ለሶማሊያ መንግሥት የመጀመሪያ ዙር ወታደራዊ ድጋፏ ማድረጓን አስታውቋል ፤ ሁለተኛው ዙር የወታደራዊ ድጋፍ ደግሞ ወደ ሀገሪቱ ዋና ከተማ ሞቃዲሾ መድረሱን አመልክቷል።

በተመሳሳይ ሮይተርስ የዜና ወኪል በበኩሉ ሁለት የወደብ ሠራተኞች እና ሁለት ወታደራዊ ባለሥልጣናት ነግረውኛል ብሎ እንደዘገበው፤ በሶማሊያ በርካታ መሣሪያዎች ከግብፅ የጦር መርከቦች ተራግፈው ፤ የመከላከያ ሚኒስቴር ህንፃ እና በአቅራቢያው ወዳሉ የጦር ካምፖች መወሰዳቸውን አስታውቋል ፡፡

ግብፅ ቀጣናውን ወዳልተገባ ቀውስ ለመክተት እየሄደች ያለችውን ርቀት የሚያሳየው ሌላኛው የሆርን ኦፍ አፍሪካ ዘገባ ፤ የግብፅ እና የሶማሊያ የነሀሴ ወር ስምምነት እስከ 10,000 / አስር ሺህ / የግብፅ ወታደሮችን በሶማሊያ ማስፈርን ያካተተ ነው ሲል ፅፏል፡፡

የሆርን ዘገባ ሲቀጥልም በሞቃዲሾ ከተማ የሚገኘው የግብፅ ኤምባሲ ማናቸውም የግብፅ ዜጎች ከሶማሊ ላንድ ባስቸኳይ እንዲወጡ እና ወደ አካባቢው ለመጓዝ ያሰቡም ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ማሳሰቡን ዘግቧል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትን አቋም ያካተተው የኢንተርናሽናል ፖሊሲ ዳይጀስት ዘገባ በበኩሉ "ኢትዮጵያ ወረራን ለሚያስቡ ሁሉ በጠቅላይ ሚኒስትሯ በኩል ቆራጥ ማስጠንቀቂያ ሰጠች" ሲል አስነብቧል ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ኢትዮጵያን ለመውረር ያሰበ ማንኛውም ሃይል በቅድሚያ አስር ጊዜ ማሰብ አለበት፡፡" ብለው ተናግረዋል ሲል አስነብቧል፡፡

ዘገባው ቱርክ እና ሌሎች የቀጣናው ሀገራት ኢትዮጵያ እና ሶማሊያን ለማደራደር ጥረት ላይ ናቸው ሲል፣ ጅቡቲ ወሳኙን የታጁራ ወደብ ለኢትዮጵያ በጨረታ ለመስጠት ሃሳብ ማቅረቧን በትንታኔው አካትቶ ነበር ፡፡

አሁን ላይ የአፍሪካ ቀንድን እና የቀይ ባህርን ጉዳይ ቆም ብሎ ላጤነው ፣ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ፤ ለቀጣናው ሀገራት አዲስ የግጭት ስጋት ይዞ የመጣ ነው። በተለይም ግብጽ በአካባቢው እያደረገች ያለው ያልተገባ ጣልቃ ገብነት አካባቢውን ወደ አለመረጋጋት ሊያመራው እንደሚችል በስፋት እየተነገረ ነው።

ችግሩን በአግባቡ የተረዱ የሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት አካል የሆኑ ክልሎች የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት እየሄዱበት ያለው የተሳሳተ መንገድ ለሶማሊያ ሕዝብ አስቸጋሪ ጊዜያትን ከማምጣት ባለፈ ትርጉም ያለው ጥቅም እንደማይኖረው እያሳሰቡ ነው። የተነጣል ርምጃዎችንም እንዲወስዱ እያስገደዳቸው ነው።

የሀገሪቱ ፕሬዚዳን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት በመከላከያ ሠራዊቱ በኩል ለሶማሊያ ሕዝብ የከፈለውን መስዋእትነት በአደባባይ ለማሳነስ የሚያደርጉትን ጥረት በመቃወም ፤ ከመከላከያ ሃይሉ ጋር ያላቸውን አጋርነት በግልጽ እያሳዩ ፤የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የክፉ ቀን ወዳጅ መሆኑም እያስታወቁ ነው ።

የሶማሊያ ሕዝብ በአክራሪ እና ጽንፈኛ ሃይሎች ሕይወቱ አደጋ ውስጥ በነበረበት ወቅት የግብፅ መንግሥት የት ነበር ? የግብፅ ወደ ሶማሊያ የማማተሯ እውነታ የዓባይ ወንዝን ጉዳይ ወደ ሶማሊያ ይዞ የመምጣት የጥፋት ስትራቴጂ ነው ፤ይህ ደግሞ የሶማሊያ ሕዝብ አጀንዳ አይደለም የሚሉ ድምጾችን ጎልተው እየተሰሙ ነው።

ዓለም አቀፉ ህብረተሰብም ቢሆን በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያለውን የአክራሪ እና ጽንፈኛ ሃይሎች እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ኢትዮጵያን ያገለለ አካሄድ የማያዋጣ መሆኑን በመግለጽ፤ የሶማሊያ መንግሥት ሁኔታዎችን በስክነት እንዲመለከተው፤ ችግሮች በድርድር እንዲፈቱ እያመላከተ ነው።

የሶማሊያ መንግሥት ኢትዮጵያ የባህር በር በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለማግኘት ያላትን የሕግ እና ሞራል መብት ተግባራዊ ለማድረግ እየሄደችበት ያለው መንገድ በአግባቡ ሊያስበው ይገባል ፤ጉዳዩ የማንን ም ጣልቃ ገብነት የማይፈልግ፤ ከሁሉም በላይ የሀገራቱን ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት መሠረት በማድረግ ሊፈታ የሚችል ነው። ለዚህ የሚያስፈልገው ካልተገባ ሆሆይታ ወጥቶ በስክነት እና በወዳጅነት መንፈስ ጉዳዩን ማጤን ነው ።

# ኮሌጁ በህትመት ዘርፍ የሚታየውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ክፍተት ለመሙላት እየሠራ ነው

## - በህትመት ቴክኖሎጂና ግራፊክስ አርት 51 ተማሪዎች አስመረቀ

**አማን ረሺድ**



አዲስ አበባ፡- በህትመት ዘርፍ የሚታየውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ክፍተት ለመሙላት እየሠራ መሆኑን ብርሃንና ሰላም የህትመት ቴክኖሎጂ ኮሌጅ አስታወቀ፡፡ ኮሌጁ በህትመት ቴክኖሎጂና ግራፊክስ አርት 51 ተማሪዎችን በትናትናው ዕለት አስመርቋል፡፡

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሽታሁን ዋለ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ህትመትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማከናወንና በህትመት ዘርፉ የሚታየውን የሠለጠነ የሰው ኃይል ክፍተት ለመሙላት ኮሌጁ የተለያዩ የሙያ ሥልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ሽታሁን ገለጻ፤ ኮሌጁ ከማሠልጠን ባለፈ ለህትመት ድርጅቶችና ለዩኒቨርሲቲዎች በህትመት ቴክኖሎጂ ዙሪያ የማማከርና የህትመት ማሽን ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሀገራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው። ተመራቂዎቹ ለሶስት ዓመታት በህትመት ቴክኖሎጂና ግራፊክስ አርት በደረጃ ሶስት ትምህርታቸውን የተከታተሉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ድርጅቱ ለበርካታ ዓመታት ያካበተውን የህትመት ሥራ ልምድ በመጠቀም የድርጅቱ ሠራተኞችን ብቃት ለማሳደግ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ባገኘው የሥልጠና ፍቃድ መሠረት ከድርጅቱ ውጪ ለሚመጡ ሠልጣኞች ሥልጠና ዕድል በማመቻቸት ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሶስት ሥልጠና በመስጠት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ከመቅረፍ አኳያ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የህትመት ቴክኖሎጂ ኮሌጅ ዲን አቶ መስፍን ካሳ በበኩላቸው ኮሌጁ በአጫጭር ጊዜ ሥልጠናዎች በህትመት ቴክኖሎጂ፣ በግራፊክ ዲዛይንና አርት፣ በህትመት ዋጋ ትመና እና በሲልክ ስክሪን የሙያ ዘርፎች በርካታ ሠልጣኞችን ማስመረቁን ገልጸዋል።

ኮሌጁ ከ2017 ዓ.ም ጀምሮ በቪዲዮ ኤዲቲንግና አኒሜሽን ሙያ አዲስ የሥልጠና ፕሮግራም ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ተናግረዋል።

ኮሌጁ በሀገር ደረጃ ብቸኛ የህትመት የሙያ ብቃትና ምዘና ማዕከል በመሆን እያገለገለ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

ኮሌጁ ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ከተለያዩ ድርጅቶች የተላኩ ባለሙያዎችንና የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ልጆች በህትመት እና በግራፊክ ዲዛይንና አርት በነጻ ሥልጠና መስጠቱን አመላክተዋል፡፡

በኮሌጁ በደረጃ ሶስት የተመረቁ ሠልጣኞች ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ የተሰማሩ መሆናቸውን ገልጸው፤ ይህም በሙያው የሠለጠነ የሰው ኃይል ተፈላጊነትና የኮሌጁን የሥልጠና ጥራት አመላካች ነው ብለዋል፡፡

ተመራቂዎቹ በበኩላቸው፤ በሀገራችን በህትመት ዘርፍ የሚታየውን የሙያ፣ የፈጠራና የንድፍ ክፍተት ለመሙላት የበኩላችሁን ለመወጣት የሚያስችላቸውን ሙያዊ ክህሎትና ዕውቀት መቅሰማቸውን ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ተመራቂዎች የህትመት ዘርፉን በማሳደግ ሂደት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የህትመት ቴክኖሎጂ ኮሌጅ በ2007 ዓ.ም እንደተቋቋመ ታውቋል፡፡

# ፍትሃዊነትን የማስፈን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለማስኬድ ተደራድረው ስድስቱ ሀገራት ማእቀፉን አጽድቀዋል፡፡ ስድስቱ ሀገራት የተፋሰሱን ማእቀፍ ስላጸደቁ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን ሊቋቋም ተቃርቧል፡፡

ኮሚሽኑ ሲቋቋም የተፋሰሱ ሀገራት ውሃ አጠቃቀማቸውን ለየሀገራቱ በሚጠቅምና ሌሎችንም በማይጎዳ መልኩ በሥርዓት መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ ለማበጀት በጋራ የሚሠሩበት መሆኑን የሚገልጹት ፕሮፌሰሩ፤ ኮሚሽኑ ሲቋቋም ለኮሚሽኑ በተዘጋጀው ሥርዓት መሠረት የልማትና ትብብር ሥራዎች ይተገበራሉ።

ከዚህ በፊት የዓይል ተፋሰስ ሀገራት በጋራ ስምምነት ያበጁት የአሠራር ማእቀፍ እንዳልነበረው አስታውሰው፤ አሁን ግን የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉን ያጸደቁ ሀገራት የናይል ተፋሰስ ኮሚሽን ለማቋቋም የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በዚህም የተፋሰሱ ሀገራት በአንድ ላይ የሚመሩበት ርእሳነ መንግሥታቱ ጉባዔ ይቋቋማል ያሉት ምሁሩ፤ በዚህ ስር ደግሞ ውሃ ሚኒስትሮች ጉባዔ ይቋቋማል፡፡ ከየሀገራቱ የተውጣጣ የውሃ ሚኒስትሮች አማካሪ ምክር ቤትም ይቋቋማል፡፡ ከዚህ በታች ደግሞ የዘርፍ አማካሪ ቡድኖች ይቋቋማሉ፡፡ እንግዲህ ይህ ሁሉ በአንድ ላይ የውሃውን አጠቃቀም እያንዳንዱ ሀገር በግዛቱ ውስጥ ውሃውን በጥቅም ላይ ሊያውል ይችላል፡፡ ነገር ግን በየሀገራቱ ጥቅም ላይ የሚውለው ውሃ የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ጉልህ በሆነ መልኩ እንዳይጎዳ ጥንቃቄ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል ይላሉ፡፡

ይህም ሀገሮች ውሃውን በየሀገራቸው ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም እንዲችሉ እና በመካከላቸው ህብረትና ትብብር እንዲኖር ያዛል፡፡

ግብጽ ማእቀፉን ለማበጀት በተደረገው ድርድር ለ11 ዓመታት አብራ ተጉዛ እንደነበር የሚቁሙት ፕሮፌሰሩ፤ መጨረሻ ከዚህ ቀደም እንደነበረው ውሃውን በእኛ የበላይት ካላስተዳደርን ወይም ከዚህ በፊት የያዝነው የውሃ አጠቃቅም ካልቀጠለ በሚል ወጥተዋል፡፡

ነገር ግን ግብጾች ቢወጡም ስድስት ሀገሮች ያጸደቁትት ዘጠኝ ሀገራት ተደራድረው ያቋቋሙት የሰነድና የአሠራር ሥርዓት ስለሆነ ሌሎች የውሃውን ሀብት ፍትሃዊነት በሆነ መንገድ ከመጠቀም ወደ ኋላ ሊሉ አይችሉም ይላሉ፡፡

እንደ ፕሮፌሰሩ ገለጻ፤ ግብጽ አኩርፋ ብትወጣም ወደ ግብጽ የሚሄድ ውሃ ስምምቱን ካጸደቁ ሀገሮች ፈልቆ የሚሄድ ስለሆነ በተለይም ከኢትዮጵያ የሚሄደው 86 በመቶ የሚሆነው ወደ ግብጽ የሚሄደው ውሃ ግብጽ ለመጠቀም ከፈለገች በትብብር እንጂ በአስገዳጅነት እንደማይሆን ሀገሮች በአጠቃላይ በተለይም ኢትዮጵያ አረጋግጣለች። ይህ ማለት ግብጽ ብትቃወምም ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች የተፋሰሱ ሀገራት መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር መሥራት የሚያስችል ሥርዓት ተፈጥሯል፡፡

ማዕቀፉን የተቃወሙ ሀገሮች በተለይ ግብጽና ሱዳን ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ እየሠራ ያለችውን ግድብ በመቃወም አፈንግጠው ቆመዋል የሚሉት ተመራማሪው፤ ይህ ደግሞ የተፋሰሱን ትብብርም ሆነ የተፋሰሱ ሀገራት የሚያደርጉትን የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት ወደ ኋላ መቀልበስ አይችሉም። የሚኖራቸው ምርጫ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በፍትሃዊነት መጠቀም እንጂ ለብቻዬ ልጠቀም የሚባልበት ዘመን አልፏል ነው ያሉት፡፡

ይህም ትብብርም በሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከርና ዘላቂ ልማታቸው ላይ አትኩረው እንዲሠሩ ያዛል ይላሉ፡፡

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሰርቬይንግና ካርታ ኢንጅነሪንግ መምህር ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን ኤርዱኖ በበኩላቸው፤ ማእቀፉ ከመኖሩ በፊት በተናጠል የተደረጉ ነገሮች ሁሉ በጥርጣሬ ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። በዚህም አንዱ አንዱን ለማጥፋት በሚደረግ የፖለቲካ ድራማ ላይ የተመሠረተ አካሄድ ሲስተዋል ቆይቷል፡፡

የትብብር ማዕቀፉ የትኛውንም ሀገር ሳይበድል ወይም ሳይጠራጠር የውሃ ዋስትናው የሚከበርበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህም በፖለቲካና በኢኮኖሚ ያለው ጠቀሜታ ብዙ ነው ይላሉ፡፡

ሁሉም የተፋሰሱ አባል ሀገራት በባለሙያ የተደገፈ ትንተና ተካሂዶ የየሀገራቱ ፍላጎት ምን ያህል እንደሆነ ታውቆ ውሃው ጥቅም ላይ እንዲውል መሥራት እንደሚያስፈልግ የሚጠቅሱት ምሁሩ፤ ግብጽ በዓለም ከሚታወቀው ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ ካላቸው ሀገራት አንዷ ናት፡፡ ነገር ግን ማውራት አትፈልግም ሙሉ በሙሉ በዓባይ ጥገኛ ነኝና አትንኩብኝ ትላለች፡፡ ይህን አጀንዳ ማቆምና በምን መልኩ በትብብር መጠቀም እንደሚቻል ማሰብ መቻል ይርባታል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የሌሎች ሀገሮች ሕዝብ እያደገ በሄደ ቁጥር በዓባይ ወንዝ የመጠቀም ፍላጎት እጨመረ እንደሚሄድ መገንዘብ ያስፈልጋል የሚሉት ዶክተር ኢንጅነር ጥላሁን፤ የግብጽ ያረጀ እሳቤ የሚያበቃበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡ ግብጽ በዚህ ግትር አቋሟ የምትቀጥል ከሆነ ከአባል ሀገራቱ የሚገጥማት ተቃውሞ እየጨመረ መሄዱ አይቀርም ነው ያሉት፡፡

የዓባይ ውሃ 86 በመቶ አምጪ ኢትዮጵያ ናት የሚሉት ምሁሩ፤ ግብጽ በትብብር ለመሥራና በፍትሃዊነት መጠቀም ሲገባት ሁሌም ኢትዮጵያን በጠላትነት ፈርጃ ለውድቀቷ ስትሠራ መኖሯ አስገራሚ ነው፡፡

የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ትብብር መጠናከር ሀገራት ያላቸውን ሀብት በፍትሃዊነት እንዲጠቀሙ እድል የሚፈጠር መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ እውን እንዲሆን ግን ግብጽ የመሰሉ አትንኩብኝ የሚል የተሳሳተ እሳቤ ያላቸው ሀገራት የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ ያስፈልጋል። አንድ በመቶ የውሃ አስተዋጽኦ የሌላት ሀገር 86 በመቶ የውሃ አበርክቶ ያላትን ሀገር ተመልካች ለማድረግ መሞከር በምንም መልኩ ተቀባይነት የሌለው ተግባር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

እንደ ምሁሩ ገለጻ፤ ባለፉት ዓመታት የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማእቀፍ ባለመኖሩ አንዱ አንዱን ለማጥፋት በሚደረግ የፖለቲካ ድራማ ላይ የተመሠረተ አካሄድ ይስተዋል ነበር፡፡ የትብብር ማእቀፉ መኖሩ አንዱ ሀገር ሌላኛውን ሀገር ሳይበድል የውሃ ዋስትናው የሚከበርበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ግብጽም የምታራምደውን የእኔ ብቻ የሚል ያለፈበት እሳቤ ትታ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር በትብብር መሥራት ይኖርባታል፡፡

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን ለምን ተጠቀመች ተብሎ የሚመጣባትን ጠላት ለመመከት መላው ኢትዮጵያውያን በአንድነትና በትብብር መመከት እንዳለባቸው የሚጠቁሙት ምሁሩ፤ ግብጽ ዛሬ ኢትዮጵያ ላይ የምታደርሰው ጫና የሚሳካላት ከሆነ ነገ ወደ ሌሎችም የተፋሰሱ ሀገራት መዞሯ አይቀርም፡፡ ከዚህ አኳያ ሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት የትብብር ማዕቀፉ በአግባቡ እንዲተገበር መሥራትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከኢትዮጵያ ጎን መቆም እንዳለባቸውም ይገልጻሉ፡፡

# የአእምሮ ህመምና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መዛግብት ይገልጻሉ፡፡ በኢትጵያም ይህ ህመም በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠው በተለያየ ጊዜ ሲነገር የሚሰማ ሲሆን ለዚህ ማሳያውም በሀገሪቱ ከ1930 ዓ.ም ጀምሮ የአእምሮ ህክምና የሚሰጠው ተቋም የአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብቻ መሆኑ ነው፡፡

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ገለፃ፤ በአሁኑ ጊዜ 970 ሚሊዮን የዓለማችን ሕዝብ በአእምሮ ህመም ይሰቃያል፡፡ እንዲሁም በየዓመቱ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በአእምሮ ህመም ምክንያት እራሳቸውን የሚያጠፉ ሲሆን በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ካሉ አራት ሰዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ በሕይወት ዘመኑ የአእምሮ ህመም ያጋጥመዋል፡፡

ለአእምሮ ህመም ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዮች መሀከል አንዱ የሥራ ቦታ አለመመቸት ሲሆን እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርትም ከ 10 እስከ 15 በመቶ የሚሆነው የአእምሮ ጤና መታወክ እንደ ምክንያትነት ይጠቀሳል። በሥራ ላይ ከሚገኘው 60 በመቶ የዓለም ሕዝብ ለአእምሮ ጤና መታወክ መንስኤ ለሆነው የሥራ ላይ አደጋ የመከላከል ርምጃ አስቸኳይ ምላሽ የሚሻ መሆኑም በሪፖርቱ ተጠቅሷል፡፡

የዓለም የአእምሮ ጤና ቀን በየዓመቱ መስከረም 30 ቀን ታስቦ የሚከበር ሲሆን የዚህ ዓመት የዓለም የአእምሮ ጤና ቀን « በሁሉም የሥራ ቦታ ቅድሚያ ለአእምሮ ጤና » በሚል መሪ ቃል ተከብሮ ውሏል፡፡

በአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የድንገተኛ ህክምና ዳይሬክተር ዶክተር ሉሉ በቃሉ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ለአእምሮ ጤና ህክምናና እክብካቤ የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ በርካቶች ህመሙ እየታየ በጊዜ ወደ ህክምና ተቋማት አይሄዱም፡፡

ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ቤተሰብ ፣ የሰፈር ሰው እንዲሁም የሥራ ባልደረባ ስለ ህመሜ ብነግራቸው መገለል ሊደርስብኝ ይችላል ከሚል አስተሳሰብ ፣ ምልክቶችን ባለማስተዋልና በአጠገባቸው ባሉ ሰዎች ርዳታ ማጣት መሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ዶክተር ሉሉ፤ ደህንነቱ ያልተጠበቀና ጤናማ ያልሆነ የሥራ አካባቢ ለአእምሮ መቃወስ አንዱ ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ፤ ባልተመቻቸ የሥራ ቦታና አካባቢ መሥራት የአእምሮ ጤናን ከማወክ ባሻገር አጠቃላይ ሕይወትን በማወክ እራሳቸውን እንዲሁም በዙሪያቸው ባሉ ሰዎች ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር መሆኑ ይገልጻሉ፡፡

የተዛባ የአእምሮ ጤና ለዝቅተኛ የሥራ ውጤት ይዳርጋል የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በዓለማችን በድባቴና በጭንቀት ብቻ በዓመት በአማካኝ 12 ቢሊዮን የሥራ ቀናት እንደሚባክን የተለያየ ጥናቶች እንደሚሳዩ ይጠቅሳሉ፡፡ በኢትጵያም በዚህ ስሜት ምክንያት ወደ ጤና ተቋማት እየሄዱ ፍቃድ የሚጠይቁ ሰዎች ቁጥር ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡

ይህም ሰዎች በሥራ ቦታዎቻቸው ደስተኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ለሚመጣ የአእምሮ መታወክ አንዱ ምልክት ነው፡፡ በሥራ ቦታ ላይ የአእምሮ ጤናን ለማጎልበት፣ የሠራተኛውን ጤናና ደህንነት መጠበቅ የቀጣሪዎች፤ የሠራተኛ ተወካዮች እንዲሁም የመንግሥት ኃላፊነት መሆን እንደሚገባው ይገልጻሉ፡፡

በሥራ ቦታ ላይ ለሚፈጠር የአእምሮ መታወክ በአብዛኛው መንስኤው የሥራ ጫና ፣ አነስተኛ ክፍያ፣ ረጅም ጊዜ መቀመጥንና የመሳሰሉት መሆናቸውን ገልጸው፤ ለዚህም መንግሥት እነዚህን ጫናዎች ሊቀንሱ የሚችሉ ፖሊሲዎች ማዘጋጀት እንደሚኖርበት ይመክራሉ፡፡

ሌላው በተቋማት ውስጥ የሚታየው ችግር ሠራተኞች የአእምሮ መታወክ ሲያጋጥማቸው ከሥራ የማሰናበት ሁኔታ እንደሚስተዋል ይጠቁማሉ፡፡ ነገር ግን የአእምሮ ህመም ያለባቸው ሠራተኞች ሲኖሩ ከማግለልና ከሥራ ከማስወጣት ይልቅ ህመማቸውን በመረዳት ጫና መቀነስና መከታተል እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

ሌላው በጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን የሰጡት የሥነልቦና ባለሙያ አቶ እንዳለ ማሞ እንደሚሉት፤ ለአእምሮ ጤና መጠበቅ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የሥራ አካባቢ አንዱ ነው፡፡ ያለ አዕምሮ ጤና ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት የማይታሰብ በመሆኑ እንደ ሀገር ለአእምሮ ህመምና ህክምና የሚሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው፡፡

በዚህም ሰዎች ህመሙ ሲስተዋልባቸው ወደ ጤና ተቋማት ከመውሰድ ይልቅ ወደ ተለያዩ የእምነት ቦታዎች እንዲሄዱ እንደሚደረግ ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን ጎን ለጎን ወደ ህክምና ተቋማት መውሰድ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ለአእምሮ ህመም ከሚያጋልጡ ቦታዎች አንዱ የሥራ ቦታ አለመመቸት በመሆኑ የሥራ ቦታዎች ጽዱ ፣ ማረፊያ ቦታዎች ያላቸው እንዲሁም ተቋማት የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ቢኖራቸው ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል ያብራራሉ፡፡

# የሕይወት ገጽታ

# በውጣ ውረድ ያልተበገረ ስኬታማ የሕይወት ጉዞ

**መክሊት ወንድወሰን እና ሰሚራ በርሀ**

«ቆራጥነት እና በዓላማ መጽናትን ሰዎች ከእርሷ ሊማሩ ይገባል» ሲሉ ባለቤታቸው ይመሰክሩላቸዋል። በልጅነታቸው ተወልደው ያደጉባትን ከተማ፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ የሚወዱትን ትምህርታቸውን እና ትምህርት ቤታቸውን ትተው ነበር ወደ አዲስ አበባ የመጡት፡፡ የተሳቡበት ትምህርት እና ለሱ ሲሉ የከፈሉለት ዋጋ ዛሬ ላይ ትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል፡፡

በልጅነታቸው የመሰረቱትን ትዳር የትምህርት ፍላጎታቸውን ሳይጫን፤ ትዳራቸው ለልጅነት ሕልማቸው ይበልጥ ድጋፍ ሆኖላቸዋል፡፡ ሕልማቸውን ማሳካት፣ የትዳር ሕይወታቸውን ማሳመር እንዲሁም ልጆቻቸውን በስኬታማ መልኩ ማሳደግ ችለዋል፡፡

ለትምህርት የነበራቸው ፍቅር እና የተጓዙበት መንገድም ወደ አስር የሚጠጉ ዓለም አቀፍ ጆርናሎችን እስከማሳተም አድርሷቸዋል፡፡ የተለያዩ ተቋማትን በብቃት መርተዋል፣ በመምህርነትም ረጅም ዓመት አገልግለዋል፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ስርዓት ትምህርትን ቀርጸዋል። በተጨማሪም የሚሰሩበትን የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲን መዋቅር ሰርተዋል፡፡ እኚህ ትጉህ ሴት ዶክተር አብረኸት መሓሪ ናቸው፡፡ በዛሬው የሕይወት ገጻችን የዶክተር አብረኸት መሓሪ የሕይወት ጉዞ ልናጋርችሁ ወደናል፡፡ መልካም ንባብ ...

## ልጅነት በብዘት ከተማ

ትውልዳቸው በትግራይ ክልል አዲግራት ከተማ ውስጥ የምትገኝ ብዘት የምትሰኝ አውራጃ /ቦታ ናት። ለወላጆቻቸው አራተኛ ልጅ ሲሆኑ ፈጣን እና በትምህርታቸው ጎበዝ ነበሩ፡፡ ለዚህም ማሳያ እድሜቸው ለትምህርት ደርሶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጀመሩ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ያለውን በመምህራኖቻቸው ምስክርነት እና በእሳቸው ውጤት በወቅቱ በነበረው የትምህርት ስርዓትና ሕግ አንዳንድ ክፍል እያጠፉ ወደቀጣዩ ክፍል ሊሸጋገሩ ችለዋል፡፡ « በልጅነቴ መሆን እፈልግ የነበረው የተለያዩ ጥናቶችን በማጥናት እና በትምህርቴ ስኬታማ ሴት መሆን ነበር፡፡ ከዚያም በእውቀት ላይ የተመሰረተ ቢዝነስን የምታንቀሳቅስ ሴት መሆን የዘወትር ሕልሜ ነበር፡፡ » የሚሉት ዶክተር አብረኸት ወላጆቻቸው በንግድ ስራ የተሰማሩ መሆናቸውንም በማስታወስ ነው።

በአብዛኛው የሀገራችን ገጠራማ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ወደ ከተማ ተጉዘው እና ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ለመማር ይገደዳሉ፡፡ ዶክተር አብረኸትም የስድስተኛ ክፍልን ትምህርታቸውን እንደጨረሱ የቀጣዩን ክፍል ትምህርት ለመማር ከአዲግራት ከተማ 37 ኪሎ ሜትር ተጉዘው ወደ ዋናው አውራጃ መጓዝ ነበረባቸው፡፡

በዚያም ሁለት ታናናሽ ወንድሞቻቸውን ይዘው ቤት ተከራይተው ትምህርታቸውን ቀጠሉ፡፡ በሳምንቱ መጨረሻም ወደቤተሰቦቻቸው በማቅናት ለሳምንታት የሚሆናቸውን ቀለብ ይዘው በመመለስ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ፡፡ ታላቅ እህት እንደመሆናቸው ጠዋት ለወንድሞቻቸው ቁርስ አዘጋጅተው ሲመለሱም ቀድመው ወደቤት በመግባት የሚቀመስ እያዘጋጁ ይጠብቋቸዋል፡፡

በሚማሩበት ትምህርት ቤትም ወላጆቻቸው በገዙላቸው ብስክሌት ይመላለሳሉ፡፡ ትምህርት ልጅነታቸው የሰጡለት ሕልማቸው ነበር፡፡ የእረፍት ክፍለጊዜያቸውን እንደሌሎች ተማሪዎች ከእኩዮቻቸው ጋር ሳይሆን ከመምህራኖቻቸው ጋር ነበር የሚያሳልፉት። የአብረኸት ወላጆች በንግድ ስራ ውስጥ ያሉ ነበሩና ለልጆቻቸው ወጪዎችን ለመሸፈንም ሆነ ትምህርታቸውን ለማስተማር ጥሩ ገቢ ነበራቸው፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ በብዙ መልክ የተሻለ ኑሮን እንዲኖሩ መደገፍና ማገዝ የሁሉም ወላጅ ተግባር ነው፡፡ ልጅን መዳር እና ለወግ ማብቃት የቤተሰብ የዘወትር ሕልም ነው፡፡ ዶክተር ልጅ በበነበሩበት ግዜ እና ዘመን ደግሞ ልጅን ሳይጠነክር መዳር የተለመደ ባሕል ነበር፡፡ ታዲያ ወላጆች ልጆቻቸውን ለዘመናት ከኖሩበት ባሕል እና አስተሳሰብ ጋር ማስታረቅ ይከብዳቸዋል፡፡ የዶክተር አብረኸት ወላጆች እና ከልጃቸው ጋር አለመስማማት ውስጥ የገቡትም በዚሁ ምክንያት ነበር፡፡

## ልጅህን ለልጄ

ትዳር ሰዎች በሕይወታቸው ሊያሳኩት ከሚገባ



ፎቶ- በረሀን ታደሰ

**አብረኸት መሓሪ ዶ/ር**

አንዱ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ታዲያ በአሁን ሰዓት ሙሉ ሙሉ ቀርቷል ለማለት ባይቻልም ከዓመታት በፊት ግን ሴት ልጆች ልክ እንደ አሁኑ እድሜያቸው ለትዳር ደርሶ፣ ፍላጎታቸው ተጠይቆ ሳይሆን ቤተሰብ ለቤተሰብ ተጠያይቆ ልጅህን ለልጄ በሚል ልጆቻቸውን ለትዳር ያጫሉ። በትዳር የመዛመድ ጥያቄ የቀረበላቸው የሴት ቤተሰብም በሀሳቡ ከተስማሙ እና ዝምድናውን ካመኑበት ጥያቄውን ተቀብለው ለልጃቸው ባል የሚሆነውን ሰው በእጮኝነት ተቀብለው ቃል ይገባሉ፡፡

አብረኸትም በዚህ ባሕል ውስጥ ማለፍ የግድ ብሏቸው ነበር፡፡ በአሁን ሰዓት የትዳር አጋራቸው የሆኑትን በእጮኝነት ወላጆቻቸው ሲመርጡላቸው ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ነበሩ፡፡ ጊዜው ደርሶ ትዳር ለመመስረት ሲበቁም የ10ኛ ክፍል ተማሪ ናቸው፡፡ ታዲያ ይህ መረጃ ለሙሽራዋ ለአብረኸት እንግዳ መረጃና በፍጹም የማይስማሙበት ነበር፡፡

« በጊዜው ለማግባት በፍጹም ፍቃደኛ አልነበርኩም። ምክንያቱም ትምህርቴን መማር እፈልግ ነበር፡፡ እንደማገባ ከተነገረኝ ጊዜ ጀምሮ በጣም አለቅስ ነበር፡፡ በሰርጌ ቀንም ተደብቄ ለመጥፋት ሞክሬ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ » የሚሉት አብረኸት ከዚያ በፊትም ልጃችሁን ለልጃችን የሚል ጥያቄ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ለቤተሰቦቻቸው ቀርቦላቸው ነበር፡ ፡ ወላጆቻቸው ግን «ቅድሚያ ትምህርቷን ትማር »በማለት ሲመልሱ አይተዋል፡፡ የአሁኑ ባለቤታቸው የአቶ ክንፈ ግርማይ ቤተሰቦች ግን ዶክተር አብረኸትን ትምህርታቸውን እንዲማሩ እንደሚያግዛቸው ለወላጆቻቸው ቃል በመግባት ጋብቻ እንዲፈጸም እንዳደረጉ ያስታውሳሉ፡፡

የሰርጉ ቀንም ሲደርስ እሳቸው በጣም አዝነው እያለቀሱ እንደነበረም ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን ከቤተሰብ ቃል እና ትዕዛዝ መውጣት ስለማይችሉ ጋብቻው ተፈጸመ፡፡ ባለቤታቸው አቶ ክንፈ ቃላቸውን በማክበር ትምህርት እንዲማሩ ፈቅደው ያስተምሯቸው ነበር፡፡

ዶ/ር አብረኸት የሀገር አቀፍ ፈተናን በሚወስዱበት ጊዜ የመጀመሪያ ልጃቸውን ነፍሰጡር ነበሩ። ነገር ግን ሕልማቸው የነበረውን ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም መግባት የሚያስችል ውጤት በጊዜው አላመጡም፡፡ ግን የመጀመሪያ ልጅ እናት መሆን ችለዋል ፤ የልጃቸውን ስምም « ሐቨን » ብለው ሰየሙት ቃሉ የትግርኛ ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም መመኪያዬ የሚል ነው፡፡ ምንም እንኳን እንደእኩዮቻቸው ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ባይችሉም ልጆቻቸው ግን መመኪያቸው መኩሪያቸው መሆኑን ለማስታወስ ነው፡፡

**በ14 ዓመታቸው ትዳርን ሲመሰርቱ ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበሩ። አሁን ላይ የአራት ልጆች ወላጅ ናቸው፡፡ በትምህርታቸው ደግሞ አንድ ዲፕሎማ፤ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ፤ አንድ ሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ ሶስተኛ ዲግሪ አላቸው**

## በአዲስ ስፍራ የሕይወት ጉዞና ሕልም

የአብረኸት ባለቤት አቶ ክንፈ ስራቸው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሰው እንዲሰሩ የሚያደርግ ነበርና ኑሯቸውን ከትግራይ ክልል ወደ አርሲ ነገሌ አደረጉ፡፡ በመሆኑም የአብረኸት ወደፊት ኑሮም የተወለዱበት እና ያደጉበትን አከባቢ ትተው ወደ ነገሌ ሄዱ፡፡ ከባለቤታቸው ጋርም በዚያው መኖር ጀመሩ። ዶክተር አብረኸት ወደ ማያውቁት ቦታ ሕይወትን ለመጀመር ሲያስቡ እንደተጓዥ ሻንጣቸውን አላዘጋጁም፤ ይልቅስ ደብተሮቻቸውን ይዘው ነበር ከትውልድ ሀገራቸው የወጡት፡፡ ከዚያም በሻሸመኔ ያጡትን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ለማሻሻል ወደኋላ ተመልሰው የመሰናዶ ትምህርታቸው በድጋሚ ከተማሩ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሜርስ ኮሌጅ መማር የሚያስችላቸውን ውጤት አሳኩ፡፡

በዚህ መሀል አብረኸት (ዶ/ር) ሁለተኛ ልጃቸውን ወልደው ነበር፡፡ ከዚያም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ልጆቻቸውን ይዘው ጉዟቸውን ወደ አዲስ አበባ አደረጉ፡፡ በአዲስ አበባም ቤት ተከራይተው ትምህርታቸውን ቀጠሉ፡፡ ብዙዎች የትዳር ሕይወት እና ራስን በትምህርት የማሻሻል ሕልምን ማስቀጠል አልታደልንበትም አልያም በእኩል ማስኬድ አልቻልነውም ሲሉ ዶ/ር አብረኸት ግን በኮሜርስ የንግድ ስራ ኮሌጅ ትምህርታቸውን ሲማሩ ሶስተኛ ሴት ልጃቸውን ነፍሰጡር ነበሩ፡፡ «ሴት ልጄን እንደወለድኩ በዘጠነኛው ቀን ከአራስ ቤት ወጥቼ ፈተና ተፈትኛለሁ።» የሚሉት ዶክተር አብረኸት የሰፕላይ ቼን ማኔጅመንት ትምህርታቸውን አጠናቀው ተመረቁ ፡፡

ዶክተር አብረኸት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እንዳጠናቀቁ በኢትዮጵያ ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን የስራ ሕይወት ጉዟቸውን ጀመሩ፡፡ በስራ ቦታቸው የነበራቸው ቆይታ እጅግ መልካም እንደነበር የሚያስታውሱት ዶክተር ትምህርታቸውን ለመተው ግን አልቻሉም፡፡ በመሆኑም በመስሪያ ቤቱ ለሰባት ዓመት ያክል ካገለገሉ በኋላ በዲግሪ ፕሮግራም ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከስራ ቦታቸው ፍቃድ ጠይቀው በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በቀን መርሀ ግብር ለመማር አመለከቱ፡፡

በዚህ ጊዜ ዶክተር አብረኸት የአራት ልጆች እናት ነበሩ፡፡ ነገር ግን ትምህርት ሕይወታቸውን የሰጡለት ለራሳቸው ቃል የገቡበት ጉዳይ ነው፡፡ በባለቤታቸውም ለአማቾቻቸው ቃል የገቡበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚያም ምክንያት ትምህርት ለሚወዱት ባለቤታቸው ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር፡፡ ዶክተሯ እንደሚሉት «ከባለቤቴ ጋር ተነጋግረን ለልጆቻችን ሞግዚትና የቤት ውስጥ አጋዥ ቀጥረን፡፡ እኔ ከዩኒቨርሲቲው ወደ ቤቴ የምመለሰው እሁድ ብቻ ነበር፡፡ ነገር ግን ለልጆቼ የሚፈልጉት ነገር እንዳይጎልባቸው እጠነቀቃለሁ፡፡ »

እንዲህ እያለ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በአካውንቲንግ የትምህርት ዘርፍ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያዙ፡፡ በኋላም ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመራቂ ተማሪዎችን አወዳድሮ የመቅጠር እድል ተወዳድረው ፈተናውን በማለፍ የዩኒቨርሲቲው መምህር እና የፋይናንስ ኃላፊ ሆነው ተሾሙ፡፡ ነገር ግን በስራቸው ላይ ብቁ ሆኖ መገኘት የማይደራደሩበት ጉዳይ ነው፡፡ «የአመራር ብቃቴን ያዳብርልኛል» ያሉትን የዴቨሎፕመንታል ማኔጅመንት ትምህርት በዚያው መማር ቀጠሉ፡፡

በዚያ ብቻ ግን አላበቁም፡፡ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመማር ከስራ ቦታቸው ፍቃድ ጠይቀው ቀን ቀን እያስተማሩ ግማሽ ቀን ደግሞ በፋይናንሻል ማኔጅመንት በሚያስተምሩበት ተቋም ውስጥ ተማሩ፡፡ « ትምህርቱን እንደጨረስኩ ሙለ ሙሉ ለማስተማር ፍላጎት ስለነበረኝ ለኢንስቲትዩቱ ያለኝን ፍላጎት አሳወቅኩ ፡፡ » ዶክተር አብረኸት ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ያጠናቀቋቸው ትምህርቶችን ያላቸውን የስራ ልምድ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሰው ሀብት አስተዳደር ስራ ውስጥ በኃላፊነት የማገልገል እድሉን አገኙ፡፡ የዩኒቨርሲቲውም መዋቅር እንዲሰሩ ጥያቄ ቀረበላቸው ፤ ለአንድ ዓመት ያክልም በሰው ሀብት ስራ ክፍል ውስጥ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን መዋቅር ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በሊደርሺፕ እና ጉድ ገቨርናንስ የትምህርት ሞጁል አስተባባሪ፣ አማካሪ እንዲሁም መምህር ሆነው በኢንስቲትዩቱ ውስጥ መስራታቸውን ቀጠሉ ፡፡

የሁለተኛ ዲግሪያቸውን አጠናቀው በሚያስተምሩበት በዚህ ወቅት የጥናትና ምርምር ወይም የሪሰርች ክፍል ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። የኢንስቲትዩቱ የሊደርሺፕ አመራር ዳይሬክተር ለመሆን የቀረበውን የውድድር መስፈርት አሟልተው እና ተወዳድረው በማሸነፍ የኢንስቲትዩቱ ዳይሬክተር ሆነው ተሾሙ ፡፡

በስራቸው ከተለያዩ ሀገራት ወደ ኢንስቲትዩቱ የሚመጡ ምሁራንን እንዲሁም የስራ ኃላፊዎች የማግኘት እድል ነበራቸው፡፡ ከቀረቡላቸው የተለያዩ ሀገራት ጥሪዎች መካከል የአዘርባዣን አምባሳደር በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ ተማሪዎችን ለማነጋገር በመጡበት ለዶክተር አብረኸት የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት እድል በአዘርባጃን እንዲማሩ እድሉን ሰጧቸው፡፡ የትምህርት እድሉ የቀረበው በኢንስትዩቱ ውስጥ ለሚገኙ ሶስት ተወዳዳሪዎች በመሆኑ ዶክተር አብረኸት ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመወዳደር እና የአንደኛ ደረጃ በመያዝ ከሌሎች ሁለት ባልደረቦቻቸው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## በውጣ ውረድ ያልተበገረ ...

ከገጽ 6 የዞረ

ጋር በመሆን በኢኮኖሚክስ የትምህርት ዘርፍ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ለማጥናት በአዘርባጃን እድል አገኙ ::

### ቤተሰባዊነት

የዶክተር አብረኸት ልጅነት ለትምህርት፤ የወላጆቻቸው ሀሳብ እና በቀደመው ባሕል ደግሞ ወደ ትዳር መመስረት አምርቷቸው ነበር :: በ14 ዓመታቸው ትዳርን ሲመሰርቱ ገና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበሩ፡፡ አሁን ላይ የአራት ልጆች ወላጅ ናቸው። በትምህርታቸው ደግሞ አንድ ዲፕሎማ፤ ሁለት የመጀመሪያ ዲግሪ፤ አንድ ሁለተኛ ዲግሪ እና አንድ ሶስተኛ ዲግሪ አላቸው፡፡ እነዚህ የትምህርት ደረጃዎች፤ ከ20 ዓመት በላይ የቆየ የማስተማር እና የአስተዳደር የስራ ልምድ ልጆች ከወለዱ በኋላ ያረጋገጧቸው ስኬቶች እና የተጓዙበት መንገድ ነው። ታዲያ ይህ ጉዞ በአንድ እናት እይታ እንዴት ይገለጻል፤ ምን ያህል ከባድ ነው ማሳካትስ ለሌሎች የሚቻል ነው ወይ? ተብሎ መጠየቁ የማይቀር ነው፡፡ ዶክተር አብረኸት እንዲህ ይላሉ « ከባለቤቴ ጋር ስንጋባ እስከመጨረሻው እኔ እስፈለኩ ድረስ ትምህርት ሊያስተምረኝ ቃል ስለገባ በማንኛውም መንገድ ላይ ደጋፊዬ ነው :: ይህንን ሁሉ ትምህርት ስማርም የቤቴን ነገር ችላ የምል አይነት ሴት አይደለሁም :: » በማለት የነበራቸውን የሰዓት አጠቃቀም ይገልጻሉ፡፡ በየዓመቱ የጥቅምት ወር ሲሆን ለቤታቸው የሚያስፈልጋቸውን አስቤዛ ለአንድ ዓመት ያክል የሚሆናቸውን አስፈጭተው አዘጋጅተው ያስቀምጣሉ ::

### ተምሳሌት

ዶክተር አብረኸት የአራት ልጆች እናት ናቸው። ከ20 ዓመት በላይ የቆየ የስራ ልምድ አላቸው፡፡ ልጆቻቸው የእርሳቸውን ፈለግ የተከተሉ ናቸው፡፡ «በልጅነቴ ስለወለድኳቸው አብረን ስንወጣ እህታቸው እንጂ እናታቸው አልመስልም፡፡ » የሚሉት ዶክተር አብረኸት፤ ለልጆቻቸው አርአያ መሆን መቻላቸውን አንስተው ጎበዝ ተማሪዎች እንደነበሩ ይገልጻሉ። ልጆቻቸው በአጠቃላይ በስራ ላይ የሚገኙ ሲሆን በትምህርታቸው እናታቸውን ፈለግ በመከተል ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ድረስ የቀጠለ ልጅ አላቸው። በአብዛኛው ልጆቻቸው ትምህርታቸው በውጭ ሀገር ተከታትለው በስራ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

ታዲያ ዶክተር አብረኸትም ነፍሰጡር በሆኑበት ጊዜም ሆነ ወልደው ትምህርታቸውን አላቋረጡም፡፡ ልጆቻቸው የውጭ ሀገር የትምህርት እድል አግኝተው ከቤት ሲወጡ፤ ዶክተሯ ከባለቤታቸው ጋር ቤት ውስጥ ቀሩ፡፡ ከዚህ ወዲያ «የሚያለቅስ፤ የማሳድገው ሆነ የማዝለው ልጅ የለኝም፡፡» በማለት ራሳቸውን አበርትተው ቀጣይ ትኩረታቸውን ራሳቸውን በትምህርት ማሳደግ እና ስራቸው ላይ አድርገዋል፡፡

« የመጀመሪያ ልጄ ከሀዋይ ዩኒቨርሲቲ በፋርማሲ ሶስተኛ ዲግሪ (ፒ.ኤች.ዲ) ይዟል፡፡ በአሜሪካን ሀገር እየሰራ ይገኛል፣ ሁለተኛ ልጄ በሳይኮሎጂ ተመርቃ በሚኖሶታ በስነ-ልቦና አማካሪነት እየሰራች ትገኛለች፣ ሶስተኛ ልጄ እንዲሁ በዓለም አቀፍ ተቋም ውስጥ እየሰራች ሲሆን የመጨረሻው ልጄ ፊዝዮቴራፒስት በመሆን እየሰራ ይገኛል እና ልጆቼ በጣም ያግዙኛል፡፡ አንዳንዴም መማር አይበቃሽም እንዴ ይሉኛል »

### የማይታለፉ የሚመስሉ ቀናት

«በሕይወት ውስጥ የማይታለፍ ችግር አለ ብዬ አላስብም፡፡» የሚሉት ዶክተር አብረኸት ዓላማቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ የሚወዱትን ትምህርታቸውን መቀጠል እና ማጠናቀቅ ነበርና የተንገዳገዱባቸውን ጊዜያት ያስታውሳሉ :: « ባገባሁበት ወቅት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ወቅት ነበርና እና ዩኒቨርሲቲ ይገባሉ ተብለው ከሚጠበቁ ተማሪዎች መካከል ስለነበርኩ በወቅቱ ያን ውጤት ማምጣት ባለመቻሌ ያለቀስኩትን መቼም አልረሳውም፡፡ »

ሌላኛው ፈተና ደግሞ በስራው ዓለም ላይ የገጠማቸው ፈተና ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውሀ ስራዎች ኮርፖሬሽን የሰራተኛ ማሕበር ተወካይ በነበሩበት ወቅት የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ በስራ ባልደረባቸው በቀረበላቸው የሀሰት ደረሰኝ እንዲያወራርዱ ተጠይቀው ነበር፡፡ ይህንንም ሃሳብ ውድቅ በማድረጋቸው ሌላ ባለሙያ ለመምረጥ በሚደረገው ምርጫ ላይ ስማቸውን የማጥፋትና በሀሳባቸው ከማይስማሙ ሰራተኞች በተለያየ መንገድ ትንኮሳ ይደርስባቸው ነበር፡፡ በምርጫው ወቅት በተደረገ ስብሰባ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ስራዎችን ለማስኬድ ከሰራተኞች የተሰበሰበን ገንዘብ አሳልፌ አልሰጥም በማለታቸው ይሄ ሁሉ በደል እንደደረሰባቸው ለኦዲተሮች እና ለኃላፊዎች አስረድተው ያን ወቅት ማለፋቸውን ይገልጻሉ ::

ዶክተር አብረኸት ማንኛውንም ፈተና አልፈዋለው የሚል ሀሳብ አስቀድመው ለራሳቸው ነግረውታል። በአዘርባጃን የፒ.ኤች.ዲ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ባቀኑበት በተሰጣቸው እድል ትምህርታቸውን ተምረው ቢጨርሱም በሀገሪቱ ሕግ ግን እንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲሁም የሀገሩን የአዘርባጃን ቋንቋ ተምረው መፈተን የግድ ይላቸው ነበር፡፡ ይህ መረጃ አስቀድሞ ያልነበራቸው አብረኸት ለአንድ ዓመት በራሳቸው ወጪ ቋንቋውን ተምረው ተፈትነው ዲግሪያቸውን ሊቀበሉ ችለዋል፡፡

### አመራርነት እና ሴትነት

ስራቸውን ሲጀምሩ በመምህርነት የጀመሩት ዶክተር አብረኸት ያጠኑት የፋይናንስ ትምህርት በመሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገለገሉበት ኃላፊነት የፋይናንስ መምሪያ ኃላፊነት ነበር፡፡ በስራቸው አንድ መርህ አላቸው፡፡ «በእውቀት አምናለሁ ከትምህርት ባሻገር የተለያዩ መጽሀፎችን አነባለሁ፡፡ ሴቶች በአመራርነት ዘመናቸው ምን ሊገጥማቸው ይችላል? የሚለውን በስራዬ እንዳልሳሳት የሚጠቅመኝን አነባለሁ፡፡ » ባጠኗቸው የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች እንዲሁ የመመረቂ ጽሁፎቻቸውን በተቋማት በውሳኔ አሰጣጥ ሒደት ውስጥ የሴቶች ሚና ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። « ሌላው ሰዎች በስራቸው ራሳቸውን ለማሳደግ ወደ ላይ ወደ ኃላፊዎቻቸው ሳይሆን ከጎናቸው ካለ ሰው መማር ስራቸውን በየጊዜው መገምገም ይገባቸዋል፡፡ አብሯቸው ከሚሰራ ሰው ጋር በፍቅር እና በመረዳዳት መስራት ይገባቸዋል፡፡

አብዛኛዎቹ ሴቶች ወደ አመራርነት ሲመጡ ይፈራሉ አቅም ኖሯቸውም ውድድር በሚኖርበት ጊዜ ራሳቸውን ያገላሉ፡፡ ያ መሆን የለበትም ውስጣቸው ሙሉ መሆን አለበት፡፡ በራስ መተማመን ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የሰው ልጅ የትም ሊያደርሰው የሚችለው ያለው በራስ መተማመን ነው፡፡ ውስጣቸው ሙሉ እንዲሆን ደግሞ ማንበብ እና መመራመር ያስፈልጋል፡፡ » ይላሉ፡፡

ዶክተር አብረኸት ኃላፊነት ሲሰጣቸው አመራር ምን ቁልፍ ነገሮችን ማሟላት አለበት? መሪዎች ለምን ይወድቃሉ? የሚለውን በማንበብ እና የማኔጅመንት ትምህርትን በመማር የአመራርነት ብቃታቸውን በማሳደግ ላለፉት ዓመታት በርካታ ስኬቶችን ማስመዝገብ ችለዋል፡፡

ዶክተሯ የማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ከፍተኛ አማካሪ ሲሆኑ ለተከታታይ 12 ዓመታት በፋይናንስ ስርዓት የማማከር ስራ ሰርተዋል፡፡ በተጨማሪም የስርዓተ - ጾታ እና ሴቶችን የማሰልጠን ስራ እየሰሩም ይገኛሉ፡፡ በዚህም ልምዳቸው ሴቶች ራሳቸውን ለማብቃት እና ወደፊት ወጥተው ለመታየት ፍርሀት እንዳይዛቸው ራሳቸውን ማብቃት ላይ እንዲሰሩ ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፡፡

ዶክተር አብረኸት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በማኔጅመንት ክፍል በኃላፊነት ሲሰሩ፤ አርብ አርብ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ለ15 ደቂቃ ያክል ስራን በጋራ የመገምገም ልምድ አላቸው። በወቅቱ በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ የሚገኙት መምህራን ይህ ጉዳይ ምቾት አልሰጣቸውም፡፡ ዶ/ር አብረኸት ምንም እንኳን በወቅቱ ኃላፊ ቢሆኑም የነበራቸው ግን ሁለተኛ ዲግሪ ብቻ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ለመቀጠል መወሰናቸውን ያስታውሳሉ።

### ጥናትና የምርምር ውጤቶች

ዶክተር አብረኸት መምህር ሆነው ላለፉት 20 ዓመታት አገልግለዋል፣ የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ በዳይሬክተር ደረጃ የመምራት እድልም አግኝተዋል። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ተማሪዎች የሚሰሯቸውን የመመረቂያ ጽሁፎችም እንዲሁ በማማከር ስራ ተሳትፈዋል፡፡ አሁንም በስራ ላይ ይገኛሉ፡፡ ታዲያ በእነዚህ ሁሉ ዓመታት በጾታ እኩልነት ፣ በክላስተር ዙርያ፣ በማኑፋክቸሪክ፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡ ከአስር በላይ የሚሆኑ የጥናት ውጤቶችን ሰርተዋል፡፡ እነዚህን የጥናት ውጤቶችም ለማቅረብ በተለያዩ ሀገራት ላይ ተዘዋውረዋል፣ ስልጠናዎችን ለመውሰድ በስራ አጋጣሚ በርካታ ሀገራትን ለማየት ችለዋል፡፡

### መምህርነት

«ማስተማር እጅግ በጣም ነው የምወደው፡፡ እውቀትን ማስተላለፍ የሕሊና እርካታ አገኝበታለሁ፤ ብዙ እንዳነብ አድርጎኛል፡፡ ልምድም አገኝበታለሁ፡፡ ከተማሪዎቼ የጎደለኝን እሞላለሁ፡፡ ከሰዎች እተዋወቃለሁ እስካሁን ድረስ ቤተሰብ የሆንኳቸው ተማሪዎች አሉኝ፡»

ዶክተር አብረኸት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ለ20 ዓመታት ሲቆዩ በማስተማር ረጅም ዓመት ልምድን አካብተዋል፡፡ ከሀገር ውስጥም ከውጭም የተለያዩ የስራ እድል ጥያቄዎች ሲቀርቡላቸው አንድም መምህርነትን በመውደዳቸው አንድም ደግሞ ሀገራቸውን በጣም በመውደዳቸው እና ከሀገር ለመውጣት ባለመፈለጋቸው አሁንም ድረስ በማስተማር ስራ ውስጥ ይገኛሉ፡፡

### አጋርነት በተግባር

ዶክተር አብረኸት ባለፉት ዓመታት በነበራቸው የስራም ሆነ የትምህርት ስኬታቸው እዚህ የደረሱበት ደረጃ በቤታቸው ያለው ሰላም እና የባለቤታቸው ያልተቋረጠ አጋዥነት መሆኑን ያነሳሉ፡፡ « ባለቤቴ በንግድ ስራ ውስጥ የተሰማራ በመሆኑ በትምህርት ብዙም አልገፋበትም፡፡ እስከ ዘጠነኛ ክፍል ብቻ ነው የተማረው፡፡ ነገር ግን በጣም ደጋፊዬ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው አንድን ሕልሙን ለማሳካት እና ያሰበበት ለመድረስ በመጀመሪያ በቤቱ ውስጥ ሰላም፣ መግባባት መረዳዳት ሊኖረው ይገባል፡፡ ካልሆነ ግን ምንም እንኳን ቆራጥ ብንሆን ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ በቤታችን ውስጥ ያለውን ችግር መፍታት እና አጋራችን የጉዟችን ደጋፊ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ቤታችን ሰላም ሲሆን ነው ውጪ ባለን ስራ ስኬታማ ልንሆን የምንችለው፡፡ »

የዶ/ር አብረኸት ባለቤት አቶ ክንፈ ግርማይ ይሰኛሉ፡፡ ለዚህ ቃለመጠይቅ ስለባለቤታቸው ያላቸው የእርሳቸውን ሀሳብ አካትተነዋል ታዲያ የነበራቸውን ትውውቅ እንደዚህ ያስታውሳሉ፡፡ « ልጆች ሆነን አንድ አካባቢ ስለነበርን አብረን ተምረናል፡፡ እኔ ደግሞ የሚማር ሰው በጣም ነው የምወደው፡፡ በዛ ላይ እኔ እንኳን ባልፍ ስለልጆቼ ሳስብ እሷ መማር እንዳለባት አምንበታለሁ፡፡ »

አቶ ክንፈ በቤታቸው ውስጥ ያሉ የቤት ሰራተኞቻቸው ጭምር ሁለተኛ ዲግሪ እንዲይዙ ማድረጋቸውን ገልጸዋል። ባለቤታቸው አብረኸት ትምህርታቸውን እየተማሩ ከጎን ልጆች እየወለዱ ነበርና ባለቤታቸው ትምህርታቸው እንዳይቋረጥ ተከታትለው ያስመዘግቧቸው ነበር፡፡ ባለቤታቸውን እንደሚያስመዘግቡ ያዩ ሰዎች እንዴት ፈቀዱላቸው በማለት እጅግ እንደሚገረሙ ያስታውሳሉ ::

ለዶክተር አብረኸት ዓላማ መሳካት የአቶ ክንፈ ሚና የሚናቅ አይደለም፡፡ ባለቤታቸው የዩንቨርሲቲ ትምህርታቸውን ሲካተተሉ እሳቸው ልጆቻቸውን ለማሳደግ ለዓመታት የፊልድ ስራቸውን ትተዋል፡፡

ዶክተር አብረኸት ትምህርታቸውን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በሚማሩበት ወቅት አቶ ክንፈ ልጆቻቸውን ትምህርትቤት በማድረስ፤ ሁኔታቸውንም በመከታተል ለዶክተር ሀሳብ ያቀሉላቸው ነበር። በባለቤታቸው የትምህርት ውጤትም እጅግ ይኮሩባቸዋል :: « ልጅ እየወለዱ መማር ፣ ማህበራዊ ሕይወት መምራት፣ ስራ መስራት በጣም ከባድ ነው፡፡ ይህን ሁሉ አቻችላ ነው የኖረችው፡፡ በይበልጥ ደግሞ ቆራጥ ናት ከዓላማዋ ዝንፍ አትልም፡፡ »የሚል ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡



**በጾታ እኩልነት ፣ በክላስተር ዙርያ፣ በማኑፋክቸሪክ፣ የአንድ መስኮት አገልግሎት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡ ከአስር በላይ የሚሆኑ የጥናት ውጤቶችን ሰርተዋል። እነዚህን የጥናት ውጤቶችም ለማቅረብ በተለያዩ ሀገራት ላይ ተዘዋውረዋል፣ ስልጠናዎችን ለመውሰድ በስራ አጋጣሚ በርካታ ሀገራትን ለማየት ችለዋል**

# ባህልና ቱሪዝም

# ሰላም- ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር ያለው አንድምታ

**ዳግም ከበደ**

አገራት በቱሪዝም ዘርፍ የላቀ ውጤት የሚያስመዘግቡት ባላቸው የመስህብ ብዛት ብቻ አይደለም። ከቱሪዝም የሚገኝ የሀብት መጠናቸው የሚያድገው፣ ለመጎብኘት ተመራጭ የሚሆኑት መዳረሻዎችን በማልማታቸው፣ በበቂ ሁኔታ በማስተዋወቃቸው ብቻም አይደለም።

ከፍተኛ የጎብኚዎች ፍሰት የሚያስተናግዱ የዓለማችን ቀዳሚው አገራት ተፈላጊነት በሚሰጡት መስተንግዶና ባላቸው ቅንጡ ሆቴሎች ብዛትና በእንግዳ ተቀባይነታቸውም አይደለም። እነዚህ አገራት የጎብኚዎችን ቀልብ ስበው፣ በየዓመቱ ሚሊዮኖች ወደ አገራቸው የሚተሙበት ዋንኛ ምክንያት ለቱሪስቶች በሚሰጡት የደህንነት ዋስትና እና በአገራቸው ባለው የሰላም አየር ምክንያት ነው።

በእርግጥ ቀልጣፋና ጥራት ያለው መስተንግዶ፣ ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ በቱሪስቶች ተመራጭ የመስህብ ስፍራ፣ የታሪክ፣ የባሕል፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን አካባቢ ለመጎብኘትና ቆይታ ለማድረግ የሚያስችል መዳረሻ ልማት ለቱሪዝም እድገት በእጅጉ አስፈላጊና ወሳኝ ናቸው። ይሁን እንጂ ሰላምና መረጋጋት ከሌለ ቱሪስቶች ደህንነት ተሰምቷቸው ቆይታ አያደርጉም። በእነዚህ ምክንያቶች የዘርፉ ባለሙያዎች ሰላም ለቱሪዝም፤ ቱሪዝም ደግሞ ለሰላም የማይተካ ሚና እንዳላቸው ይናገራሉ።

አቶ ገዛኸኝ አባተ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስትቲዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ናቸው። በኢትዮጵያ ለ37ተኛ ጊዜ ‹‹ቱሪዝምና ሰላም ›› በሚል መሪ ሀሳብ የተከበረውን የዓለም የቱሪዝም ቀን በማስመልከት ተቋማቸው ባዘጋጀ የፓናል ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ ሰላምና ለቱሪዝም ተመጋጋቢና አንዳቸው ለአንደኛቸው በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው። ሰዎች ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እና የመስህብ ስፍራዎችን ለመጎብኘት፣ አገልግሎት ሰጪዎችም የጎብኚዎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ የተሟላ መስተንግዶ ለማቅረብ ሰላም በእጅጉ ያስፈልጋል። በዚህ ምክንያት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያለው ቱሪዝም እንዲነቃቃ ለማድረግ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

የኢንስትቲዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ቱሪዝም በከተማና በገጠር ያለውን የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ለማጠናከር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ይጠቁማሉ። ዘርፉ የስራ እድል ለመፍጠር ካለው ከፍተኛ አቅም ባሻገር ታሪካዊ፣ ባሕላዊ፣ ተፈጥሯዊ ሀብቶችን ለመጠበቅ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ፍልሰት ለመቀነስ የሚያስችል ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ መሆኑንም ያመለክታሉ።

ያልተነካ እምቅ አቅም ያለው በመሆኑም በእቅድ ከተሰራ አስተማማኝ የስራ እድልና ሀብት የሚፈጥር መሆኑ እንደሚታመንም ይናገራሉ። ዘርፉ ካለው የአካታችነት ባህሪ አንፃር በመንግስት፣ በግሉ ዘርፍና በሲቪክ ማህበረሰቡ መካከል ሊኖር የሚገባውን የትብብርና የስራ ጥምረት የማጎልበት አቅም እንደሚፈጥር አስገንዘበዋል።

ቱሪዝም ከዚህ የአካታችነት ባህሪው ባሻገር የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን በአንድነት በማሰባሰብ ማህበራዊ መስተጋብራቸው እንዲጠናከር፣ የባህልና የኢኮኖሚ ትስስር እንዲፈጠር እንደሚያደርግ የሚናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለዚህ ሰላም በእጅጉ ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ። ሰላምና መረጋጋት ለቱሪዝም እድገት ወሳኝነት እንዳለው ተናግረው፤ በተቃራኒው ቱሪዝም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል የሚያካትት እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጆች የባህል ልውውጥ እንዲያደርጉና በመካከላቸው መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር በማስቻል ለሰላም መስፈንም የበኩሉን እንደሚወጣ ጠቁመዋል። ከዚህ አንፃር

**ሰላምና ቱሪዝም ተመጋጋቢና አንዳቸው ለአንደኛቸው በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው:: ሰዎች ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እና የመስህብ ስፍራዎችን ለመጎብኘት፣ አገልግሎት ሰጪዎችም የጎብኚዎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ የተሟላ መስተንግዶ ለማቅረብ ሰላም በእጅጉ ያስፈልጋል:: በዚህ ምክንያት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋፆኦ ያለው ቱሪዝም እንዲነቃቃ ለማድረግ ሰላምና ደህንነትን ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል**

ሁሉም የመስኩ ባለድርሻዎች ኢትዮጵያ ከዘርፉ የምታገኘውን ጥቅም ለማሳደግ ሰላም ለቱሪዝም፤ ቱሪዝም ደግሞ ለሰላም የሚኖራቸውን ሚና ለማሳደግ መረባረብ ያስፈልጋል ይላሉ።

አቶ ሳህለ ተክሌ የሆቴልና ቱሪዝም ማኔጅመንት ምሁር ናቸው። በጥናትና ምርምር እንዲሁም በማማከር ለበርካታ ዓመታት ሰርተዋል። የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ‹‹ሰላምና ቱሪዝም›› በሚል ርእሰ ጉዳይ ላይ ባዘጋጀው ፓናል ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል። እርሳቸውም፤ ሰላምና ቱሪዝም የማይነጣጠሉ አንዳቸው ለአንዳቸው በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆኑ ይገልፃሉ።

ለቱሪዝም እድገት ሰላም ያለው ከባቢ መኖሩ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠውና አስፈላጊ ነው የሚሉት ጥናት አቅራቢው፤ ሰዎች ከቦታ ቦታ በነፃነት ለመንቀሳቀስ የመስህብ ስፍራዎችን ለመጎብኘት እንዲሁም መስህቦቹ የሚገኙባቸው ቦታዎችም እንግዶችን ተቀብለው ለማስተናገድ ሰላም አስፈላጊ እንደሆነ ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ የቱሪዝም እድገት መኖሩ በራሱ ሰላም እንደሚያመጣ፣ ሰዎች የስራ እድል ሲፈጠርላቸው፣ ማህበረሰቡ የኢኮኖሚ አቅሙን ባሉት የመስህብ ሀብቶች ሲያሳድግ በተመሳሳይ ለሰላም መኖር አስተዋፆኦ እንደሚያበረክት ይናገራሉ።

‹‹ቱሪስቶች በቀላሉ ሰላም እንዳለ ሊገምቱ የሚችሉባቸው አገራትን ተመራጭ ያደርጋሉ›› የሚሉት ጥናት አቅራቢው አቶ ሳህለ ተክሌ፤ ማንኛውም ቱሪስት በደህንነቱ እንዲሁም ምን ሊፈጠርበት እንደሚችል እርግጠኛ ወዳልሆነበት አካባቢ ለጉብኝት መሄድ ምርጫው እንዳልሆነ ያስረዳሉ።

ቱሪዝም ከሌሎች ዘርፎች በተለየ በትንሽ አለመረጋጋትና ሰላም እጦት ተፅእኖ ስር የሚወድቅ ፍፁም ሰላምን የሚፈልግ መሆኑንም ጠቅሰው፣ የውስጥ አለመረጋጋት፣ ደህንነትን አደጋ ውስጥ ሊከቱ የሚችሉ ስፍራዎች፣ ዘረፋ እና ሌሎች መሰል በቀጥታ ከሰላም እጦት ጋር የሚገናኙ ጉዳዮች የሚፈጠሩ ከሆነ የቱሪስቱ ፍሰትም እንደሚያሽቆለቁል አጠቃላይ የቱሪዝሙ እድገት እንደሚቀንስ ያስረዳሉ።

የሰላም እጦት በቱሪዝም መሰረተ ልማት እና በቱሪስት ፍሰት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ለመረዳት ሶሪያን፣ ግብፅን፣ ማሊን እንደ ምሳሌ የሚያነሱት ጥናት አቅራቢው፤ ሶሪያ ዘመናትን የተሻገሩ ቅርሶች በአይ ኤስ አይ ኤስ ሽብርተኛ ቡድን መውደሙና የቱሪስት ፍሰቱ በ94 በመቶ መቀነሱ እንዲሁም ኢኮኖሚ ተፅእኖው በእጅጉ ለማሽቆልቆሉ ምክንያት መሆኑን አብነት ጠቅሰው አብራርተዋል። በግብፅም በአረብ አብዮት በ2011 የቱሪስት ፍሰቱ በ95 በመቶ ቀንሶ እንደነበር አስታውሰው፣ በሲሪላንካና በማሊም በውስጥ አለመረጋጋት እና የእርስ በእርስ ግጭት ምክንያት በዘርፉ ላይ ከፍተኛ ኪሳራ እንዳደረሰ በአስረጂነት ይጠቅሳሉ።

በኢትዮጵያ የኮቪድ ወረርሽኝ በተከሰተ ወቅት ቱሪዝሙ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሮበታል የሚሉት ጥናት አቅራቢው፤ ከዚያ በተጨማሪ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ፖለቲካን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች መፈጠራቸው ለቱሪስት ፍሰት መቀነስ ምክንያት ስለመሆናቸውም አመልክተዋል።

መንግሥት ቱሪዝምን ከአምስቱ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ማድረጉና ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱ አንድ በጎ ጅምር መሆኑንም ጠቅሰው፣ በአገሪቱ የሚታየው አለመረጋጋት በቀጥታ በእድገቱ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እየፈጠረ መሆኑን ያመለክታሉ። መንግሥት በቱሪዝም ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ ሲሰራ በተቃራኒው ግጭቶች ደግሞ ለጎብኚዎችና ለዘርፉ እድገት ጋሬጣ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

በየአካባቢው የሚፈጠሩ ፖለቲካን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት የተጀመሩ መነሳሳቶች ውጤት ሲያሳዩ፣ ይህም መንግሥት ለዘርፉ እየሰጠ ካለው ከፍተኛ ትኩረት ጋር ሲደመር በቅርብ ጊዜ ውስጥ በጎ ውጤት ይመዘገባል ሲሉም ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

ጥናት አቅራቢው ኢትዮጵያ እጅግ በርካታ የተፈጥሮ፣ የባህል፣ የታሪክ እና የሌሎች የዓለም ቅርስና መስህቦች ባለቤት እንደሆነች ይናገራሉ። ይህንን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም አገራዊ እርቅ በማድረግ፣ የተረጋጋ ከባቢን በመፍጠር የጎብኚዎችን ቀልብና እምነት ሙሉ በሙሉ በማግኘት ቱሪዝም ለኢኮኖሚና ለማህበረሰብ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋፆኦ ማሳደግ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

አቶ ዳንኤል ወርቁ የኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለስልጣንን በመወከል በፓናል ውይይቱ ላይ ተሳትፈዋል፤ እርሳቸው የጥናት አቅራቢውን ፅሁፍ እና የውይይቱን ርእሰ ጉዳይ አስመልክተው በሰጡት አስተያየት እሳቸውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰላም እጦት ምክንያት በዓለማችን ላይ በበርካታ አገራት የቱሪዝም እድገትና የቱሪስት ፍሰት እያሽቆለቆለ መሆኑን ጠቅሰዋል። ከእነዚህ አገራት አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነችም ይገልፃሉ።

አንድ የቱሪዝም መዳረሻ ተወዳዳሪ የሚሆነው ከመለኪያዎቹ ውስጥ አንዱ የሆነውን የሰላምና የደህንነት መስፈርትን ሲያሟላ እንደሆነ አቶ ዳንኤል አስታውቀው፣ ሰላምን ማረጋገጥ እና ለቱሪዝሙ እድገት መሰረት መጣል ወሳኝ እንደሆነ ይናገራሉ።

ጎብኚዎች ከቤታቸው የሚወጡት ተጨማሪ ሰላምን ፍለጋ እንጂ ራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጥ ስጋት ውስጥ ለመከተት አለመሆኑን በመጥቀስ፣ ለጎብኚዎች ምቹ ከባቢ መፍጠር ቀዳሚ መሆኑን አስገንዝበዋል። አገራት በሰላም እጦት ምክንያት ከፍተኛ ኪሳራ እንደሚደርስባቸው እንደ ምሳሌ በማንሳትም ሲሪላንካ እ.ኤ.አ በ2019 ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ ከአምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማጣቷን ይጠቅሳሉ።

‹‹ሰላም ከሌለ መስህቦች ላይም ጉዳት ይደርሳል›› የሚሉት የዱር እንስሳት ጥበቃ ተወካዩ አቶ ዳንኤል፤ ይህን ተከትሎም የስራ አጥ ቁጥር እንደሚጨምር፣ የቱሪዝም እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያርፍና ድህነት እንደሚባባስ ይህም ወደ ተጨማሪ አለመረጋጋት እንደሚወስድ አብራርተዋል። በእነዚህ ምክንያቶች ሰላም ለቱሪዝም ቱሪዝም ደግሞ ለሰላም የማይተካ ሚና እንዳላቸው ጠቅሰው፣ ለእነዚህ ጉዳዮች ሁሉም ባለድርሻዎች ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባቸው አስረድተዋል።

በፓናል ውይይቱ ላይ በርካታ ተሳታፊዎች ጥናታዊ ፅሁፉን መነሻ በማድረግ አስተያየቶች ተሰጥተዋል:: የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከሚያበረክተው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አስተዋፆኦ ጋር በተያያዘ ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ እንደሚባል አስተያየት ሰጪዎቹ ጠቅሰው፣ ይሁን እንጂ በሰላም ምክንያት በሚፈጠር ስጋት ጎብኚዎች እየቀነሱ መምጣታቸውን አመልክተዋል:: ይህንን ችግር ለመፍታት በልዩ ልዩ አካባቢዎች የሚታዩ ፖለቲካዊ ችግሮችን እንደ ሽምግልና ባሉት ባህላዊ ስርዓቶች በእርቅና በመሳሰሉት በመፍታት ሰላምን መመለስና የቱሪዝሙን እድገት ማረጋገጥ እንደሚገባ ተነስቷል።

ሁሉም ዜጎች የአገራቸውን ገፅታ ሊገነባ በሚችል መልኩ የሰላም ዘብ መሆን እንደሚገባቸውም በተሳታፊዎቹ ተጠቁሟል:: ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ አንስቶ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንደሚገባው የተመላከተ ሲሆን፣ በተለይ የአገር ገፅታን ሊያጠለሹ በሚችሉ ድርጊቶች ላይ ባለመሳተፍ ለዘርፉ አስተዋፆኦ ማበርከት እንደሚገባ ተገልጧል። አንድ ጎብኚ ወደ ኢትዮጵያ በሚገባበት ወቅት ከአየር መንገድ አንስቶ እስከሚያርፍበት ሆቴል ድረስ እንዲሁም በሆቴልና የጉብኝነት ቆይታው እስኪጠናቀቅ ደህንነቱን መጠበቅ እንደሚያስፈልግ አስተያየት ሰጪዎቹ አስገንዝበዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## ድንበር ተሻጋሪው ጀግና በዛሬዋ ቀን

**ዋለልኝ አየለ**

አብዛኞቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ታሪክ ከዓድዋ እና ከአምስት ዓመቱ የጣሊያን ቆይታ ጋር ይገናኛል። ኢትዮጵያ በፋሺስት ኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት ለአገራቸው ሉዓላዊነት ታግለው አኩሪ የጀግንነት ገድል ካስመዘገቡት አርበኞች መካከል አብዛኞቹ ድል ያስመዘገቡት እዚሁ ኢትዮጵያ ምድር ላይ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ደግሞ ኢትዮጵያ የፋሺስቱን የቤኒቶ ሙሶሎኒን መንግሥት እዚያው አገሩ፣ ኢጣሊያ ላይ ተዋግተው ውርደትን ያከናነቡ ጀግኖችም ባለቤት ናት። ይህን ደማቅ ገድል ከፈፀሙ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች መካከል የዚህ ሳምንት ክስተት የሆኑት ኮሎኔል አብዲሳ አጋ አንዱ ናቸው፡፡ በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ47 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ልክ በዛሬዋ ቀን ጥቅምት 3 ቀን 1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ኮሎኔል አብዲሳ አጋን እናስታውሳለን፡፡ ከዚያ በፊት እንደተለመደው በዚህ ሳምንት የተከናወኑ ሌሎች የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ክስተቶችን እናስታውስ፡፡

እንደ ዓድዋ፣ አርበኞች ቀን፣ ካራማራ... የመሳሰሉት የድል በዓላት ሲደርሱ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ዘፈኑ በተደጋጋሚ የሚሰማው፣ የኮሪያው ዘማች እና የክራሩ ጌታ፤ ‹‹ፋኖ ፋኖ›› በተባለውና በሌሎች ተወዳጅ ሙዚቃዎቹ የሚታወቀው የክራር ተጨዋች ድምፃዊ ካሣ ተሰማ ያረፈው ከ51 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 1 ቀን 1966 ዓ.ም ነበር፡፡

ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ መስከረም 7 ቀን 1888 ዓ.ም የውጫሌ ውል እንደማይቀበሉና ሁሉም ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት እንዲከላከሉ የሚያሳስብ ታሪካዊ አዋጅ ካስነገሩ በኋላ፣ ጦራቸውን ይዘው ከአዲስ አበባ ወደ ዓድዋ ጉዞ የጀመሩት ከ129 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ነበር፡፡

አንጋፋውና ተወዳጁ አርቲስት ፍቃዱ ተክለማርያም የተወለደው ከ69 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 2 ቀን 1948 ዓ.ም ነበር፡፡

ገጣሚ፣ ሰዓሊ፣ ቀራፂ፣ ሙዚቀኛ፣ ፖለቲከኛ፣ የፎቶግራፍ ባለሙያ፣ ነጋዴ፣ ሹፌር፣ ባለቅኔ፣ የመኪና ጠጋኝ (መካኒክ) የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ከ60 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 3 ቀን 1957 ዓ.ም ነበር፡፡

አሁን በዕለቱ በዝርዝር ወደምናየው የኮሎኔል አብዲሳ አጋ ታሪክ እንለፍ፡፡

አብዲሳ አጋ የተወለዱት በ1911 ዓ.ም ወለጋ ውስጥ ነው፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም ወደ ነጆ ሚሲዮን ትምህርት ቤት አምርተው ፊደል ቆጥረዋል። ይሁን እንጂ ይህ የትምህርት ጅምራቸው ብዙ ርቀት መጓዝ ሳይችል ቀርቶ ስድስተኛ ክፍል ላይ ተገታ፡፡ ወላጅ አባታቸው ባላጠፉት ጥፋት ተወንጅለው ለእስራት በመዳረጋቸው ምክንያት አባታቸውን ከእስር ለማስፈታት ላይ ታች ሲሉ በትምህርታቸው መቀጠል ሳይችሉ ቀሩ። አባታቸው ፍትሕ እንዲያገኙ የጀመሩት ጥረትም ሊሳካላቸው አልቻለም፡፡

ወታደር ለመሆን ምኞት ያደረባቸው አብዲሳ፣ ለንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ቅርብ የሆኑ የአባታቸው ወዳጅ እንደ አማላጅ ወደ ንጉሰ ነገሥቱ ተልከው ስለ አብዲሳ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት አገኘና ታዳጊው አብዲሳ ሆለታ ወደሚገኘው ገነት ጦር ትምህርት ቤት ገብተው ስልጠና ወሰዱ፡፡

ያ የወሰዱት ሥልጠና እነሆ የአገራቸውን ነፃነት ለማስጠበቅ አገለገለ፡፡ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን ሽንፈት ለመበቀል ለአርባ ዓመታት ያህል ስትዘጋጅ ከኖረች በኋላ በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን ወረረች፡፡ ወቅቱም አብዲሳ ከገነት ጦር ትምህርት ቤት የአስር አለቃነት ማዕረግ ያገኙበት ጊዜ ነበር፡፡ ታዳጊው አብዲሳም ገና በልጅነታቸው፣ የኢትዮጵያን ጦር በመቀላቀል ሀገራቸውን ማገልገል ጀመሩ። ከወራሪው የፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ጋር ፍልሚያ የጀመሩት ገና የ16 ዓመት ታዳጊ ሆነው ሳለ ነበር፡፡

አብዲሳ ከሌሎች የገነት ጦር ትምህርት ቤት ሰልጣኞች ጋር ወደ ወለጋ በመዝመት ከፋሺስት ጦር ጋር ውጊያ ገጠሙ፡፡ በውጊያውም ወቅት መትረየስ ተኳሽ ሆነው የኢጣሊያ አውሮፕላኖችን እየመቱ ጥለዋል። ጣሊያኖችም የአብዲሳ ድርጊት ባደረሰባቸው ኪሳራ ከመበሳጨት አልፈው መገረም ጀመሩ፡፡ ጣሊያኖችም ኃይላቸውን በማጠናከር አብዲሳን ለመማረክ ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ፡፡ አብዲሳን ጨምሮ 60 ያህል የተዋጊዎች ቡድን አባላት የፀረ ፋሺስት ትግሉን ለመቀጠል ወደ ጎጀብ በማምራት ከራስ እምሩ ጦር ጋር በመቀላቀል ከጠላት ጋር ግንባር ለግንባር ገጠሙ፡፡ በዚህ ወቅት አብዲሳ በውጊያ ላይ ሳሉ የመቁሰል አደጋ አጋጠማቸውና ተማረኩ፡፡ ሕክምና ተደረገላቸውና አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ እስር ቤት ታሰሩ፡፡ ይሁን እንጂ ከመቁሰላቸው ባሻገር በጠላት መታሰራቸውን ማመንም መቀበልም ያቃታቸው ጀግናው ሰው፣ የእስር ቤቱን ጠባቂ መትረየስ ነጥቀው አመለጡ፡፡

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በኢትዮጵያ የፋሺስት ኢጣሊያ እንደራሴ የነበረውን ማርሻል ሩዶልፎ ግራዚያኒንና ሌሎች የፋሺስቱን አስተዳደር ባለስልጣናት ለመግደል በተደረገው ሙከራ በርካታ ኢትዮያጵውያን በግፍ ተጨፈጨፉ፡፡ አብዲሳም ኢትዮጵያውያንን በግፍ ሲጨፈጭፉ ከነበሩ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮች መካከል የአንዱን ቡድን አባላት ከነመኪናቸው በመትረየስ አጋዩዋቸው፡፡ ቀድሞም ቢሆን እንዲታሰሩ ተወስኖባቸው እየተፈለጉ የነበሩት አብዲሳ፣ ይህ ድርጊታቸው ሲሰማ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ፍለጋው ተጠናከረባቸውና ተያዙ፡፡ እርሳቸውና ሌሎች ግለሰቦችም በእስር ቤት በከባድ ስቃይ ውስጥ ከቆዩ በኋላ ‹‹ጀግኖችን ስታገኙ ወደ እኔ ላኩልኝ›› ብሎ ያዘዘውን ቤኒቶ ሙሶሊኒን ለማስደሰት በወቅቱ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት በነበረው የሶማሊያ ክፍል በኩል ወደ ኢጣሊያ ተወስደው ለሌላ እስር ተዳረጉ።

በእስር ቤት በነበሩበት ወቅት ካጋጠሟቸው ክስተቶች መካከል ስለ አብዲሳ አጋ የሕይወት ጉዞ በሚተርከውና ‹‹በኢጣሊያ በረሃዎች›› በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ይህ ተጽፏል፡፡

‹‹አንዲት የእንግሊዝ አውሮፕላን እኛ በታሰርንበት ወህኒ ቤት ላይ ስታንዣብብ ከቆየች በኋላ በተለያዩ ቋንቋዎች የተፃፈ ወረቀት በተነች፡፡ እኔም ወረቀቱን አንስቼ ኪሴ ውስጥ ከተትኩት፡፡ ይህን ተግባሬን የተመለከተ አንድ እስረኛ ለእስር ቤቱ ጠባቂዎች ተናገረ፤ ጠባቂዎቹም ወረቀቱን እንድሰጣቸው ጠየቁኝ፤ እኔ ግን አሻፈረኝ አልኩ፡፡ በዚህ ጊዜ እኔም ከጠባቂዎቹ መካከል አንዱን በቦክስ ስመታው መሬት ላይ ተዘረረ፡፡››

በአብዲሳ አጋ ኃይለኛነት የተጨነቁት የእስር ቤቱ ኃላፊዎችና ጠባቂዎችም አብዲሳን ለብቻቸው እንዲታሰሩ አደረጉ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር የኢጣሊያ መንግሥት ጥርስ እንደነከሰባቸው ያወቁትና ከእስር ቤት ማምለጥ እንዳለባቸው የወሰኑት፡፡

አልሸነፍ ባይነት መለያቸው የሆነው ጀግናው አብዲሳ፣ ሁሊዮ ከተባለ ዩጎዝላቪያዊ የጦር እስረኛ ጋር በመተባበር ከባድ ጥበቃ ከሚደረግበት እስር ቤት ለማምለጥ ማሰላሰል ጀመሩ። ተሳክቶላቸው ቢያመልጡ እንግዳ (ባዕድ) ሀገርና ሕዝብ እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁም፣ በነጻነታቸውና በሀገራቸው የማይደራደሩት ጀግናው የኢትዮጵያ ልጅ አብዲሳ አጋ፣ እስር ቤት ውስጥ የተሰጣቸውን የብርድ ልብስ ቀዳደው በመቀጣጠልና የእስር ቤቱ ጠባቂዎች ላይ ጥቃት በመፈፀም ሌሎች እስረኞችን በመያዝ ከእስር ቤት አመለጡ።

ከዚያ በኋላ ግን ጀግናው አብዲሳ የመረጡት ሽሽት አልነበረም፡፡ ወደ ሳን ቪቺኖ ተራራ በመውጣት ስለቀጣዩ እቅዳቸው አሰላሰሉ፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላም በማታ ወደ እስር ቤቱ በመመለስ ጠባቂዎቹ ላይ ጥቃት በመፈፀም የቀሩትን እስረኞች በሙሉ ነፃ ማውጣት ቻሉ። ነፃ የወጡት እስረኞችም ከእስር ቤቱ ጠባቂዎች በወሰዱት መሳሪያ በመታገዝ የአማፂያንን ጦር አደራጁ፤ ጦሩን እንዲመሩ የተመረጡትም ጀግናው አብዲሳ አጋ ነበሩ። በመቀጠልም የተለያዩ የኢጣሊያ ወታደራዊ ሠፈሮች ላይ ጥቃት በመፈፀም ወራሪዎቹ ጣሊያኖች ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው የአርበኞች እንቅስቃሴ ያልተናነሰ ጥቃት በሀገራቸው ያጋጥማቸው ጀመር። ‹‹አብዲሳ አጋን ማርካችሁ አምጡልኝ›› ተብለው ከሙሶሎኒ የሚላኩት የኢጣሊያ የጦር አዛዦች በአብዲሳ እየተማረኩ ቀሩ፡፡

በአራት ክፍለ ጦሮች ተከፍሎ የፋሺስትን ጦር እየተፋለመ በነበረውና በአብዲሳ አጋ በሚመራው ጦር ከባድ ኪሳራ የደረሰባቸውና እጅግ የተረበሹት ጣሊያኖችም በርካታ ስጦታዎችን ቃል በመግባት ውጊያውን እንዲያቆሙና የነሱን ጦር እንዲቀላቀሉ ለመኗቸው። የአገራቸው የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መደፈር ያንገበገባቸው አብዲሳ ግን ከፋሺስት ሥርዓት ጎን እንደማይቆሙ አስረግጠው በመናገር ጥያቄውን ውድቅ አድርገው ጣልያኖችን በሀገራቸው ማስጨነቁን ነበር ቀጠሉበት።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲጀመር የጀርመኑ ናዚ አዶልፍ ሂትለርና የኢጣሊያው ፋሺስት ቤኒቶ ሙሶሊኒ በአንድ ወገን ተሰልፈው ነበር፡፡ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ሶቭየት ኅብረትና ሌሎች ሀገራት ደግሞ ‹‹የኅብረት ኃይሎች (Allied Powers)›› የሚል የጦር ኅብረት መስርተው ጀርመንንና ጣሊያንን እንዲሁም የፋሺስቶቹንና የናዚዎቹን አጋሮች መውጋት ጀመሩ። በወቅቱም የዚህ ‹‹የኅብረት ኃይሎች›› ጦር አባላት ጣሊያኖችን እያስጨነቋቸው የነበሩትን የአብዲሳን ዝና በመስማታቸው ባላንጣቸውን ኢጣሊያን ለማዳከም በማሰብ ለአብዲሳ ጦር የቁሳቁስ ድጋፎችን ማድረግ ጀመሩ።

‹‹ከእኛ በላይ ላሳር›› ያሉት ፋሺስቶቹና ናዚዎቹም ከኅብረቱ ኃይሎች የሚሰነዘሩባቸውን ጥቃቶች መመከት ሳይችሉ ቀርተው ለመሸነፍ ተገደዱ፡፡ ከኅብረቱ ኃይሎች ባገኙት ድጋፍ እየታገዙ የፋሺስቱን መንግሥት በአገሩ አፈር ላይ የሽንፈት ማቅ ማልበስ የጀመሩት አብዲሳ አጋ፣ የፋሺስቶቹና የናዚዎቹ ቡድን ተሸንፎ የኢጣሊያዋ ዋና ከተማ ሮም በአሜሪካና በእንግሊዝ በሚመራው ጦር ቁጥጥር ስር ስትወድቅ አብዲሳ አጋ የሚመሯቸውን ከተለያዩ አገር የተውጣጡ ወታደሮች በሙሉ በክንዳቸው ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንዲያስሩ በማድረግ የአገራቸውን መለያ እያውለበለቡ ሮም ከተማ ሲገቡ በኅብረቱ ጦር ትልቅ አቀባበል ተደርጎላቸዋል።

ከዚያም በኋላ ከተጨማሪ ወታደሮች ጋር በኅብረቱ ኃይሎች የሚመራ ጦር መሪ በመሆን የናዚውን የአዶልፍ ሂትለርን ጦር በማሸነፍ ጀርመንን ከናዚዎች አገዛዝ ለማላቀቅ በሚደረገው የመጨረሻ ውጊያ ላይ ተሳትፈው ግዳጃቸውን በሚገባ መወጣት ችለዋል፡፡ በርካታ የጀርመን ከተሞችንም ከናዚዎች ነፃ አወጡ፡፡ በጦርነቱ ሂደትም አብዲሳ አጋ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ከእጃቸው ላይ ሳይለዩ መቆየታቸው ለአገራቸው ኢትዮጵያ የነበራቸውን ፍቅርና አክብሮት ያሳዩበት አጋጣሚ ነበር።

ከጦርነቱ መገባደድ በኋላም የእንግሊዝ፣ የካናዳ እና የአሜሪካ መንግሥታት አብዲሳ ጦራቸውን ተቀላቅለው እንዲቀጥሉ ዜግነት መስጠትን ጨምሮ በርካታ ጥቅማ ጥቅሞችን አቀረቡላቸው። አብዲሳ ግን ኢትዮጵያ ምንም ያህል ድሃ ብትሆንም ሕዝባቸውን እና የአገራቸውን መንግሥት ጥለው ሌላ አገር የማገልገል ፍላጎት እንደሌላቸው እንደማይሄድ አስረግጠው በመናገር የኃያላኑን መንግሥታት ጥያቄ ሳይቀበሉ ቀሩ።

አብዲሳ ‹‹የእኛን አገር ዜግነት ሰጥተንህ የእኛን ጦር ተቀላቀል›› የሚለውን የኃያላኑን መንግሥታት ጥያቄ አለመቀበላቸው ያስከፋቸው የኅብረቱ ጦር አባላት ‹‹ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ ጣሊያናውያን ላይ የበቀል እርምጃ እየወሰደ ነው›› ብለው የሐሰት ክስ ከሰሷቸውና ለእስር ተዳረጉ፤ እስራትም ተፈረደባቸው፡፡ እንግዲህ የዚህ ሁሉ የውሸት ውንጀላ ምክንያቱ አብዲሳ ‹‹በኢትዮጵያ አልደራደርም!›› በማለታቸው ነው፡፡ በኋላም እስራቱ ወደ ገንዘብ መቀጮ ተለውጦላቸው ከእስር ተለቀቁ፡፡ የሜዳሊያና የክብር መሸኛ ተሰጥተው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ፡፡

አዲስ አበባ እንደደረሱም ንጉሰ ነገሥቱ ዘንድ ቀረቡ፡፡ ንጉሰ ነገሥቱም ከነ ራስ አበበ ጋር ተነጋገሩና ‹‹ሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ሄዶ ኮርስ ይውሰድ›› ብለው ወሰኑ። ይሁን እንጂ አብዲሳ ካላቸው ልምድና ከፈፀሟቸው ጀብዱዎች አንፃር ይህ ውሳኔ ተገቢነቱ አጠያያቂ ስለመሆኑ በርካቶች ይናገራሉ፡፡

ለጉብኝት የሚመጡ የውጭ አገራት መሪዎች (የሲቪል ባለስልጣናትና የጦር መሪዎች) ስለ አብዲሳ አጋ ጀግንነትና ዝና ሲያወሩ የሰሙት ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ፣ ጀግናውን ሰው ወደ ቤተ መንግሥታቸው በማምጣት በኮሎኔልነት ማዕረግ የንጉሡ ጥበቃ ቡድን አባል አድርገው ሾሟቸው።

ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከፋሺስት ኢጣሊያ ጦር ጋር ሲፋለሙ በሰውነታቸው ውስጥ የገቡት ጥይቶች አገራቸውን በቅንነትና በታማኝነት ከማገልገል አላገዷቸውም፡፡ በ1956ቱ የሶማሊያ ወረራ ወቅትም ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ክብር አኩሪ ታሪክ ሰርተዋል። በወቅቱ በቶጎጫሌ ግንባር የ26ኛ ክብር ዘበኛ ሻለቃ የአንደኛ ሻምበል አዛዥ ሆነው የሶማሊያን ወራሪ ኃይል ተፋልመዋል፡፡

በመጨረሻም ለማመን የሚከብዱ አኩሪ የጀግንነት ገድሎችን የፈጸሙት ጀግናው ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፣ ጥቅምት 3 ቀን 1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ እነሆ ወደር የለሽ ጀግንነታቸው ሲዘከር ይኖራል!



ኮሉኔል አብዲሳ አጋ

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ጉምቱው ብዕረኛ!

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ሀገራችን በስነ-ጽሁፍ ታሪክ ቀደምት እንደመሆኗ ልዩ አሻራቸውን የጣሉ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የኪነጥበብ ሰዎችን አፍርታለች። በእያንዳንዱ ዘመንም በርካታ የጥበብ ሰዎች መጥተዋል፣ ሄደዋልም፡፡ ኢትዮጵያ መቼም ጥበበኞችን ነጥፋ አታውቅም፡፡

በዛሬው የዝነኞች ገጻችን የዚህኛው ዘመን የኪነ-ጥበብ ፈርጥ ከሆኑት መካከል ስለ አንድ ሰው የሕይወት ታሪክ፣ ዘመን አይሽሬ ከሆኑ ስራዎቹ ጋር በማጣመር ልናቀርብላችሁ ወደናል። ይህ ሰው በሰራቸው የስነ-ጽሁፍ ስራዎቹ ከአንባቢያንና ሀያሲያን ዘንድ ትልቅ አድናቆትንና ዝናን የተቸረ፣ ድንቅ በሆኑ የፈጠራና በራሱ የአጻጻፍ ስልት ልዩ ልዩ ሽልማቶችን ማግኘት የቻለ ባለ ብዙ ተሰጥኦና ድንቅ አዕምሮ ባለቤት ነው። ደራሲና ገጣሚ አዳም ረታ።

ሐምሌ 8 ቀን 1950 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተወለደው አዳም ረታ ገና በልጅነቱ በውስጡ የተጸነሰው የስነ-ጹሁፍ ዝንባሌ ዛሬ ላበረከታቸው ተወዳጅ ስራዎቹ መሰረት ጥሎለታል። በአንድ ወቅት በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ስለዚህ የተናገረውን እንመልከት፡፡ "5ኛ ክፍል እያለሁ ዓርብ ዓርብ ከሰዓት በኋላ ሪፖርት እናቀርባለን፡፡ ደንቡ ከጋዜጣ ያነበብነውን ወይም ከሬዲዮ የሰማነውን ነገር በራሳችን አማርኛ አሳጥረን ጽፈን ክፍል ውስጥ ማቅረብ ነው፡፡

ሁልጊዜ ርዕስ የሚሆኑት የጃንሆይ ጉብኝት፤ የአዲስ አበባ አንደኛ ዲቪዚዮን እግር ኳስ ውድድር ውጤት እና የመካከለኛው ምስራቅ ግጭት ነው፡፡ ነገር ግን ይህን መጻፍ ሰለቸኝ፡፡ አንድ ቀን በመንገድ ላይ ስሄድ የዶሮ ነጋዴዎች ሀይለኛ አውሎ ነፋስ መጥቶ ሲያተራምሳቸው እና ዶሮዎቹ ከቅርጫት እየበረሩ ሲያመልጡ ነጋዴዎቹም እነሱን ለመያዝ የሚያደርጉትን መውደቅና መነሳት አየሁ እና ገረመኝ። ያን ለመጻፍ ወሰንኩ፡፡ ጽፌም ክፍል ውስጥ አቀረብኩና ተማሪዎቹን ትንሽ አስደሰትኳቸው። ከዚያ መምህሩ ከየት አመጣከው ሲሉኝ ከጋዜጣ አንብቤ ነው አልኩ፡፡ ጋዜጣ ላይ እንዲህ አይነት ነገር አይጻፍም ብለው ጢሜን አበረሩኝ፡፡ ከዚያ ግን ለተማሪዎች አዳሙ ደራሲ ነው የሚሆነው ብለው ተናገሩ፡፡ ደራሲ መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያኔ አልገባኝም፡፡"

አዳም በአብዛኛው የሚጽፈው ልቦለዶችን ቢሆንም ግጥሞችንም የመጻፍ ልዩ ችሎታ አለው። ግጥሞቹ በተለያዩ ጊዜያት መፅሔቶች ላይ መታተም የቻሉ ቢሆንም ያልታተሙ ግጥሞችና የስነ-ጽሁፍ ስራዎቹ በርካታ ናቸው። በስነ-ጽሁፉ ብቻ ሳይሆን በቀለም ትምህርቱም የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ የቻለው አዳም ረታ በጂኦግራፊ የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተቀበለ ሲሆን፤ ሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በውጭ ሀገር አግኝቷል።


አዳም ረታ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ተሰጥኦው እንደ ሻማ ያበራበትና በኢትዮጵያ የስነ-ጽሁፍ ተከታታዮች እና አንባቢያን ልብ ውስጥ የመሠረት ድንጋይ ያስቀመጠበትን የበኩር ስራውን ይዞ በ1977 ዓ.ም በአንዲት መጽሃፍ ብቅ አለ። ይሄውም "አባ ደፋር እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች" የተሰኘው መጽሀፍ ነው። በዚህ የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ ውስጥ የተለያዩ ጸሐፊዎች የተሳተፉበት ሲሆን፤ ደራሲ አዳም ረታ ድብድብ፣ ዕብዱ ሺበሺ፣ ሲሮኮ እና ሲፊንክስ በድምሩ አራት ስራዎችን በመጽሃፉ ውስጥ ለማካተት ችሏል።

በ1990 ዓ.ም "ጭጋግና ጠል" የአጭር ታሪኮች ስብስብ ውስጥ "ዘላን" የተሰኘ ልቦለዱ ታትሟል። እነዚህ ሁለቱ ከሌሎች ደራሲዎች ስራዎች ጋር በጥምረት የታተሙለት በመሆኑ እንደ ወጥ ሳይቆጠሩ ቀርተዋል።

ደራሲው የመጀመሪያ ወጥ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ የሆነውን "ማህሌትን" ለመጀመሪያ ጊዜ በ1981 ዓ.ም ለማሳተም በቅቷል። ሌላው በሻማ ቡክስ በ1997 ዓ.ም የታተመው "ግራጫ ቃጭሎች" የሚለው መጽሀፉ ለአዳም ረታ ትልቅ የመሸጋገሪያ ድልድይና ልዩ ችሎታው የታየበት ወጥ ረጅም ልብወለድ ነው።

ጉዛቸውን የቀጠሉት የአዳም ረታ የማይነጥፉ



ደራሲና ገጣሚ አዳም ረታ፣

የብዕር ጠብታዎቹ በ2001 ዓ.ም አለንጋና ምስር እንዲሁም እቴሜቴ ሎሚሽታ በ2002 ዓ.ም ከሰማይ የወረደ ፍርፍር፣ በ2003 ዓ.ም ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ እና በ2004 ዓ.ም ሕማማት እና በገና በተከታታይ በየዓመቱ ታትመው ለንባብ በቅተዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ መረቅ በ2007 ዓ.ም፣ የስንብት ቀለማት በ2008 ዓ.ም ሌላው በ2010 ዓ.ም አፍ የተሰኙ በርካታ ድንቅ ስራዎችን በተለየ አቀራረብ በመስራት ለአንባቢያን እነሆ ማለት ችሏል።

በአንድ ወቅት በአዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ በከተበው ጽሁፍ ስለራሱ ሲናገር በድግግሞሽና በአንድ አይነት መንገድ መሄድ በጣም እንደሚያሰለቸው ገልጾ ነበር። ለዚህ ደግሞ ስራዎቹን መመልከት ከቻልን ወጣ ባለ በራሱ የአቀራረብ ስልት ይዞ መምጣቱ ምስክር ነው።

ቀደም ሲል "በአባ ደፋርና ሌሎች" ስብስቦች ውስጥ ስራዎቹን የማቅረብ እድል በማግኘት የጀመረው የአዳም ረታ የጥበብ ጉዞ ከስኬቶቹ ኋላ ቆየት ብሎም ሌሎች ወጣት ጸሃፊያን ፈለጉን ይከተሉ ዘንድ "አማሌሌ" በተሰኘው መጽሃፍ ላይ አብሯቸው በጥምረት ሰርቷል።

ስራዎቹ በብዛት በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሀይማኖታዊና መሰል መስተጋብሮቻችን ውስጥ በሚገኙ ቀላል በሚመስሉ እምቅ ሀሳቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ሲሆኑ፤ ኪናዊ ለዛን በተላበሰ መልኩ በጨዋታ እያዋዛ ልባችንን እንዲኮረኩሩን አድርጎ አቅርቧቸዋል። ቆም ብለን ደግሞ በጥልቀት እንድናስብና እራሳችንን እንድንመረምር ያደርገናል። የምናቡ ርቀትና ገለጻው፣ የሚያነሳቸው ሀሳቦችና የቋንቋ ሀብቱ ሁሌም አፍ ያስከፍታሉ፡፡

አዳም ነዋሪነቱ በካናዳዋ ኦታዋ ይሁን እንጂ ሀገሩን በተመለከተ የምናብ ችግር የለበትም፡፡ እንዲያውም ከሌሎች ደራሲያን በተለየ የኢትዮጵያውያንን ሁለንተናዊ ገጽታ በድርሰቱ ውስጥ እስከ ጥቃቅኗ ቅንጣት ድረስ ወርዶ በዝርዝር ይተነትናል፡፡ በአንድ ወቅት ሀልዮ ከተባለ መጽሄት ጋር በነበረው ቆይታ ይህን ሲያስረዳ "ከሀገርህ ስትወጣ ራስህን ባዶ አድርገህ አይደለም የምትወጣው፤ ሁሉን ነገር ትውስታህ ውስጥ ትይዛለህ" ብሏል፡፡ አክሎም "የትረካ ቅርጹን ነው እኔ የምፈጥረው፡፡ እንጂ በውስጡ ሊነሱ የሚችሉ ግብረገባዊ እና ሌሎች ነገሮችን እኔ የምፈጥራቸው አይደሉም፤ ዓለም የሚሰጠኝ ነው፡፡ እኔ ሕብረተሰቡ ውስጥ የምገኝ ቢሆንም በምጽፍ ጊዜ ግን ራሴን ነጥዬ ገለል ብዬ ለመመልከት እሞክራለሁ፡፡ "በማለት የአጻጻፍ መንገዱን ተናግሯል፡፡

የአዳም ረታ የብዕር ስራዎችና ሀሳቦች እንደ አባይ ጅረት የማይነጥፉና ተቀድተው የማያልቁ ግዙፍ ባህር ናቸውና እስቲ ከሰራቸው ስራዎች መሃከል ከመጽሃፉ መጽሃፍ፣ ከገጽ ወደ ገጽ እየዘለልን በጥቂቱ እንቃኛቸው።

"ባዕዳን ከፋፍሎ ሊገዛህ ሲያሴር ካልገባህ እና እንደሰራህ ከተሰራህለት በአእምሮው ስፋት በለጠህ ማለት አይደለም? ለመሆኑ እግዚአብሄር ተፈጥሮንና ሰውን እንዴት ፈጠረው? በቃሉ ትዕዛዝ ነው። ሰው ሁን አለ ሰውም ሆነ። ዛፍ ሁን አለ፤ ዛፍም ሆነ ወዘተ...... ባዕዳን ተጣሉ ሲሉን መጣላት፣ ሩጡ ሲሉን መሮጥ፣ ራቁታችሁን ሁኑ ሲሉን መሆን፣ ሁሉ ነገራችን ከዚያም ዝቅ ያለ ነው። በተለይ በፖለቲካ ሳይንሱ። (የስንብት ቀለማት)

ይህ 960 ገጾችን የያዘው የስንብት ቀለማት መጽሐፍ ራሳችንን በደንብ እንድንመለከት ይጋብዘናል፡፡ ከተወሰኑ ገጾች መሃከልም፡-

****

"የእኛ ሰፈር አዋቂ ይገርመኛል፤ ላባ አይቶ 'አሞራ አየሁ' የሚል፣ ጅና አይቶ 'አንበሳ አየሁ' የሚል፣ ጠብታ ውሃ አይቶ 'ዶፍ በዚህ አልፎ ነበር' የሚል፣ ቆዳ ቦት የሚያዘወትር ሰውዬ ቢያይ 'ወታደር አየሁ' የሚል ነው። (እነዚህን አይነቶች ፖለቲከኛ አያድርግብዎ!)

***

"የሚያስፈራኝ ደሃነትና የመንገድ መፍረስ አይደለም፡፡ የሥጋና የአጥንቴ መድከም አይደለም፡፡ የዕቃ መወደድ አይደለም፡፡ እግዜር የከፈተውን አፍ ሳይዘጋው ካደረማ፤ እግዜሩም እግዜር እኔም ሰው አይደለሁም።

**(የስንብት ቀለማት)**

***

"ፍትህ ትወዳለህ፤ ፍትህ እንደጎደለ እያወቅህ ግን ዝም ትላለህ። አየህ ይሄ አንድ ሰው ሲከፋፈል ነው።"

***

"መኖር የሚከብደው ከሰው ጋር ብቻ አይደለም፤ ከዶሮም ጋር ነው። አሁን ከጎረቤቶቼ መጣላት ብፈልግ በ'ዶሮአችሁን ሰብስቡ' ሰበብ አምባጓሮ መቀስቀስ እችላለሁ። ዋናው እውነት መሆኑ አይደለም። ደፍሮ የመዘባረቅ ነው።"

**(መረቅ)**

**"ዛሬ በትንንሽ ምሬት ይሞላና ጊዜ ይለወጣል፡፡**
**ምንም የረባ ሳይደረግ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ይራራቃሉ፣**
**የተያያዙ ይፈታታሉ፣**
**ፍቅር የገመዳቸው ይበታተናሉ፡፡**
**ሁሌም ሚስጥር ነው፡፡**
**ለምን እንደወደድንም ለምን እንዳልወደድንም ሚስጥር ነው፡፡"**
**(እቴሜቴ_ሎሚ_ሽታ)**

****

"ጠዋት እዚህ ፀሐይ ስሞቅ የቆረጥኩት የአውራ ጣቴ ጥፍር ለስንት ጉንዳን እራት ይሆናል? ባላርስም አበላሁ ማለት ነው... ሂሂሂ"

***

**''አብዮተኛ ውስጥ ቡርዧ አለ፣**
**ቡርዧ ውስጥ ፊውዳል አለ፣**
**ፊውዳሉ ውስጥ ገበሬ አለ፣**
**ገበሬው ውስጥ እረኛ አለ፣**
**እረኛ ውስጥ ላም አለ፣**
**ላሟ ውስጥ ሳር አለ፣**
**ሳሩ ውስጥ አፈር አለ፡፡**

ለሊታችን ተቆፍሮ ቢታይ ሁላችንም የምናልመው በእርግጥ አፈር ነው፡፡ ታላቅ የመሰለው፣ የረቀቀ የመሰለው ፅንሰ ሀሳብ ሁሉ በምላስ ሙጫ የቆመ የአፈር እንክብል ነው።" (መረቅ)

****

**"ይሄ ኀብረተሰብ እኔን ጎድቶኛል፡፡**
**ቁስሌን መፍጠራቸውን ረስተውታል፡፡**
**እኔ አልረሳሁትም፡፡**
**አንድ ጥፊ ሲሰጡት ሌላ የሚጠብቅ**
**ወይ ጠንካራ ጉንጭ ያለው ነው፣**
**ወይ ጅል ቅዱስ ነው"**
**(ማሕሌት)**

*****

"አዕምሮአቸው ብሩህ ባህላቸው ግን የባርያ የሆኑ ስንት አሉ በእግዜር። ባላምንበትም ልማልበት። አይ አም ኢንተለጀንት ብሎ የሚናገር ግን ዘር ማንዘሩ በቁንጫ የሚበላበት፣ በጎጥ ብራንድ የነደደ ሰው አያበሽቅህም? በ'ነኝ' ሰው የሚበላለጥ ቢሆን የዓለም ጌታዋ ብዙ ነበር። 'ውበት ሃሰት ነው ደም ግባትም ከንቱ ነው' እንደሚባለው አዕምሮም ሃሰት ነው ብልጥነትም ከንቱ ነው። ሁሉ ረጋፊ ነው።" (አፍ)

አዳም ረታ በተለየ የአፃፃፍ ስልቱ እና በስራዎቹ ጥልቀት ከአንባቢያንና የጥበብ አፍቃሪያን አድናቆትን ከማትረፉ ባሻገር ከሀገራችን ጉንቱ ሃያስያን ዘንድ አዎንታዊ ሂስ እና ምስክርነትን ማግኘት ችሏል።

ለምሳሌ ያህል ዳኛቸው ወርቁ ስለ አዳም ረታ ይህንን ብሎለታል፤ በ"አደፍርስ" የኢፒሶዲክ ሕግጋትን አጋምሶ ለማስተዋወቅ ከሞከረ ወዲህ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ በኢፒሶዲክ ተሟልቶ የተገኘ ድርሰት "ግራጫ ቃጭሎች" ነው። ... "ግራጫ ቃጭሎች" ከገፀ-ባህሪው አካልና ሥነ-ልቡና አሳሳል አልፈን ድንቅ ዓላማውን፣ ቋንቋውንና የሕይወት አተረጓጎሙን ስንመለከት የአዳም ረታ እውቀትና ልምድ ጠንከር - ጠጠር ብሎ በመዝገቡ በኩል ሲያስተጋባ ነው የምንመለከተው።...

ደራሲና ገጣሚ አዳም ረታ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ሽልማቶችን ማግኘት የቻለ ሲሆን በዋናነት በ2009 ዓ.ም

ኢስትዌስት ኢንተርቴይንመትና ኤቨንት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለመጀመሪያ ጊዜ ባዘጋጁት "ሆሄ" የሥነ ፅሑፍ ሽልማት ላይ በምርጥ የዓመቱ ረዥም ልቦለድ ዘርፍ "የስንብት ቀለማት" በተሰኘው መጽሃፉ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ርዕደ መሬት እንዴት ይከሰታል፤ እንዴትስ የሚያስከትለውን አደጋ መከላከል ይቻላል

ልጅ እያለሁ ስለመሬት መንቀጥቀጥ ሲወራ መስማቴን አስታውሳለሁ። ነፍስ ካወቅሁ በኋላ ደግሞ ከጋዜጣ አንብቢያለሁ፣ ከሬዲዮ ሰምቻለሁ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በተደጋጋሚ በቴሌቪዥን እየተመለከትሁ ነው። የመሬት መንቀጥቀጥ ነገር በተወሳ ቁጥር ቀድማ ወደ አእምሮዬ የምትመጣው ጃፓን ናት። ከዚያ ሄይቲ ናት። የስምጥ ሸለቆ ቀጣና ለመሬት መንቀጥቀጥ ተጋላጭ እንደሆነም ደጋግሜ ሰምቻለሁ።

በሕይወት ዘመን ሲከሰት አያለሁ ብዬ ግን በጭራሽ አስቤ አላውቅም። ላካ ይሄን ማሰቤ ስህተት ነበር። ባለፈው እሁድ በሕይወት ዘመኔ ለተወሰኑ ሰከንዶች በስሱ ተከስቶ አየሁት። የኮንዶሚኒየሙ ግንባታ እንደነገሩነት አካል ጉዳተኛ ከመሆኔ ጋር አሰብሁትና ፈራሁ። ራሴን ታዘብሁት። የመሬት መንቀጥቀጥ ለካ እንዲህ በአንድ ጊዜ ቅርብ ይሆናል። ይቺ የማንቂያ ድወል ናት። የሚነቃ ይንቃ። ግንባታዎቻችንንና የመሠረተ ልማቶቸን ይሄን ታሳቢ ሊያደርጉ ይገባል።

መስከረም 26 እሑድ ምሽት አዋሽ ፈንታሌ አካባቢ በሬክተር ስኬል 4.9 የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ የተከሰተ መሆኑን፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጂኦ ፊዝክስ ስፔስ ሳይንስና አስትሮኖሚ ተቋም መገናኛ ብዙኃን በሰጠው መግለጫ ይህን አረጋግጧል። እንዲሁም የአሜሪካ መንግሥት ኦፊሴላዊ የመሬት መንቀጥቀጥ ድረ-ገፅ አሁናዊ መረጃ በሚያደርስበት ገፁ መተሀራ አካባቢ መካከለኛ የሚባል የመሬት መንቀጥቀጥ መከሰቱን አስታውቋል። ንዝረቱ መዲናችንንም አዲስ አበባ ተሰምቷታል።

ምሽት 2፡10 ገደማ በርካታ የአዲስ አበባ እና የናዝሬት ከተማ ነዋሪዎች የመሬት ንዝረቱ እንደተሰማቸው በማኅበራዊ ሚዲያዎች አጋርተዋል። እኔ በምኖርበት ኮንዶሚኒየም ለጥንቃቄ በተደረገ ልፈፋ ከየቤታችን ወጥተን ሜዳ ላይ ሆነን የሚሆነውን ለመጠባበቅ ተገደን ነበር። ሁሉ በዛች ቅጽበት የሆነውን አፍ ለአፍ ገጥሞ እያወራ ነበር። የተቀረው እጅ ስልኩ ላይ ተደፍቶ ስለመሬት መንቀጥቀጡ መረጃ እየጎለጎለ ነበር።

የአሜሪካው ድረ-ገፅ እንደገለፀው፤ በአካባቢው ሰዓት አቆጣጠር ምሽት 2 ሰዓት ገደማ የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ 10 ኪሎ ሜትር ጥልቀት ነበረው። ድረ-ገፁ አክሎ ከመተሀራ ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የተከሰተው መንቀጥቀጥ ንዝረቱ ከ380 ኪሎ ሜትር ርቀት በላይ ተሰምቷል፤ ፍጥነቱም 0.48 ሰከንድ ነው ብሏል። የመሬት ንዝሩ በተለይ በአዲስ አበባ በርካታ መንደሮች የተሰማ ሲሆን ሀያት፣ ሲኤምሲ፣ ቦሌ አራብሳ፣ የካ አባዶ እና ሌሎችም አካባቢዎች ያሉ ነዋሪዎች የመሬት ንዝረት እንደተሰማቸው ተናግረዋል።

ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተለጠፉ ፎቶዎች በርካታ ነዋሪዎች በድንጋጤ ከመኖሪያ ቤታቸው ወጥተው መንገድ ላይ ሰብሰብ ብለው አስመልክተዋል። ክራይሲስ 24 የተባለው ድረ-ገፅ ደግሞ የመሬት መንቀጥቀጡ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ባሉ አካባቢዎች መሰማቱን ፅፏል። ይህን ተፈጥራዊን ክስተት የሚከታተሉ ድረ-ገፆች ከአዋሽ 23 ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ በሬክተር ስኬል 4.9 ነው፤ ይህም መካከለኛ የሚባል ነው ሲሉ ዘግበዋል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጂኦፊዚክስ እና ስፔስ ሳይንስ ክፍል ኃላፊ የሆኑት ዶ/ር ኤሊያስ ሌዊ “የመሬት መንቀጥቀጡ ለነዋሪዎች አስጊ አይደለም”ሲሉ ለመንግሥት መገናኛ ብዙኃን መግለጻቸው ይታወሳል። ባለሙያው አዋሽ ፈንታሌ አካባቢ የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ አዲስ አበባ የተሰማው ንዝረቱ መሆኑን፤ ከሰሞኑ በአፋር ክልል የመሬት መንቀጥቀጦች እንደነበሩም አረጋግጠው፤ እሑድ ምሽት በተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት በሰው እና በንብረት ላይ የደረሰ አደጋ ስለመኖሩ እስካሁን ምንም አልተሰማም። ለመሆኑ ርዕደ መሬት ማለት ምን ማለት ነው? የሚከሰተውስ እንዴት ነው? የሚለውን እንመልከት።

የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም ርዕደ መሬት በመሬት ውስጥ በታመቀ ኃይል ልቀት የተነሳ ሳይዝሚክ ሞገዶች ወይም seismic waves በሚባሉ ሞገዶች አማካኝነት የሚመጣ የተፈጥሮ አደጋ ነው። አደጋው በ ሬክታር የመለኪያ መሳሪያ የሚለካ ሲሆን ሲስሞግራፍ ወይም ሲስሞሜትርም ለመለኪያነት ያገለግላሉ። ከዚህ የተያያዙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን እንመልከት።

የአሜሪካ የጅኦሎጂካል ሰርቬይ መረጃ እንደሚያሳየው ርዕደ መሬት የሚፈጠረው የምድር ንጣፎች ወይም «ቴክቶኒክ ፕሌትስ» በሚሰኙት ጠርዝ ላይ ነው። እነዚህ የምድር ቅርፊቶች የተደራረቡ እና ሁልጊዜ በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ግን እርስ በእርስ የሚጋጩበት ጊዜ አለ። በነገራችን ላይ እንስሳት ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት እንግዳ ባህሪ ያሳያሉ። ለተረዳው እንደ ተፈጥሮአዊ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሊጠቀምበት ይችላል።

የአሜሪካ የጂኦሎጂካል ሰርቬይ መረጃ እንደሚያሳየው ርዕደ መሬት የሚፈጠረው ከምድር በታች በሚገኙ አለታማ ቁሶች ግጭት ነው። ይህ ግጭት የሚፈጠረው የምድር ንጣፎች ወይም «ቴክቶኒክ ፕሌትስ» በሚሰኙት ጠርዝ ላይ ነው። እነዚህ የምድር ቅርፊቶች የተደራረቡ እና ሁልጊዜ በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ግን እርስ በእርስ የሚተሻሹበት እና የሚጋጩበት ጊዜ አለ። ይህ ድንገተኛ ግጭት የሚፈጥረው ንዝረት እና ሞገድም ምድርን በመሰንጠቅ ርዕደ መሬት እንዲፈጠር ያደርጋል።

በዚህ ሁኔታ ጥር 29 ቀን 2015 ዓ/ም በቱርክ እና በሶርያ የተከሰተው አስከፊ ርዕደ መሬት በርካቶች ጉዳት ሲደርስባቸው ከ36 ሺህ በላይ ሰዎችንም ሕይወት ነጥቋል። በሬክተር ስኬል 7 ነጥብ 8 የተለካው ይህ ክስተት ከተሞቹንም ወደ ፍርስራሽነት ቀይሯል። ይህንን መሰሉን ተፈጥሯዊ ክስተት መከላከል የሚያስችል ሳይንሳዊ መላ ይኖር ይሆን በሚል በዶቼቬለ የተጠየቁት የባህርዳር ዩንቨርሲቲ መምህር እና የስነ-ምድር ተመራማሪ የሆኑትን ዶክተር ምንያህል ተፈሪ፤ «ርዕደ መሬትን መከላከል አይቻልም። መከላከል ሳይሆን የሚቻለው የሰው ሕይወት እንዳይጠፋ ሕብረተሰቡን ከአካባቢው ማንሳት እና ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ነው »ብለዋል።

“ነገር ግን መቼ እንደሚከሰት ትክክለኛ ጊዜ መናገር ባይቻልም ርዕደ መሬት ከመድረሱ በፊት የመሬትን የላይኛውን የአካል ክፍል እንቅስቃሴ በመመልከት ቅድመ ትንበያ ማድረግ እንደሚቻል ተመራማሪው ያስረዳሉ። «መተንበይ ይቻላል። ለምሳሌ የጃፓኑ የ2011 ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት ተተንብዮ ነበረ። በ30 ዓመት ውስጥ ይከሰታል ብለው ሳይንቲስቶች የፊዚክስ ባለሙያዎች ተንብየው ነበር። ያንን ትንበያ ባደረጉ በዓመቱ ነው የተከሰተው። ምክንያቱም የሚተነበየው የመሬትን የላይኛውን አካል እንቅስቃሴ እንደሆነ አመልክተዋል።

ርዕደ መሬት ከተፈጥሯዊ በተጨማሪ በሰው ሰራሽ መንገድ በግንባታ፣ በማዕድን ቁፋሮ እና በአቶሚክ ቦንብ ፍንዳታ ሊከሰት ይችላል። በዓለም ላይ አነስተኛ ርዕደ መሬት በየትኛውም ቦታ የሚከሰት

**ይህንን የመሬት ውስጣዊ እንቅስቃሴም ከሰዎች ይልቅ እንስሳት ቀድመው እንደሚረዱት፤ እንደ ውሻ ፣ አሳ፣ አዕዋፍ ፣ ተሳቢ እንስሳት እና ነፍሳትን የመሳሰሉ እንስሳት አውዳሚ ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት እንግዳ ባህሪ እንደሚያሳዩ፤ ይህንንም እንደ ጃፓን እና አሜሪካ ያሉ ሀገራት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እንደሚጠቀሙበት ተመራማሪው አስረድተዋል**

ሲሆን፤ ፍሎሪዳ እና ሰሜን ዳኮታ አነስተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ያለባቸው የአሜሪካ ግዛቶች ናቸው። አንታርክቲካ ከየትኛውም አህጉር ትንሹ ርዕደ መሬት የሚከሰትበት አህጉር ነው። አብዛኛው አውዳሚ ርዕደ መሬት የሚከሰተውበፓስፊክ አካባቢ ነው።

ይህ የሆነበት ምክንያትም የመሬት ንጣፍ /ፕሌቶች/ በአብዛኛው የሚንቀሳቀሱት በዚሁ አካባቢ በመሆኑ ነው። በቅርቡ ርዕደ መሬት የተከሰተባቸው ቱርክ እና ሶርያም በዚሁ አካባቢ የሚገኙ ናቸው። ባለሙያዎቹ እንደሚሉትም እነዚህ ክስተቶች የአረቢያን የመሬት ንጣፍ /ፕሌት/ ወደ ሰሜን በሚያደርገው እንቅስቃሴ ከምስራቅ አናቶሊያ የመሬት ንጣፍ /ፕሌት/ ጋር በመጋጨቱ የተፈጠረ ነው። በኢትዮጵያም የስምጥ ሸለቆ አካባቢ ለዚህ ክስተት የተጋለጠ መሆኑን ተመራማሪው ይገልፃሉ።

«ክረስት» የሚባለው የመሬት የላይኛው ክፍል «ማንትል»በሚባለው የታችኛው የመሬት ክፍል ላይ እንደሚንቀሳቀስ የሚገልፁት ባለሙያው ጠቁመው በእንቅስቃሴው በሚፈጠር ግጭት እና ንዝረትም በተለዩ ሁኔታ በርዕደ መሬት የሚጠቁ ሌሎች ሀገራት መኖራቸውንም ያስረዳሉ። ከፍ ብሎ ለመጠቆም እንደተሞከረው፤ ይህንን የመሬት ውስጣዊ እንቅስቃሴም ከሰዎች ይልቅ እንስሳት ቀድመው እንደሚረዱት፤ እንደ ውሻ ፣ አሳ፣ አዕዋፍ፣ ተሳቢ እንስሳት እና ነፍሳትን የመሳሰሉ እንስሳት አውዳሚ ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት እንግዳ ባህሪ እንደሚያሳዩ፤ ይህንንም እንደ ጃፓን እና አሜሪካ ያሉ ሀገራት የሚደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ እንደሚጠቀሙበት ተመራማሪው አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ዋናው ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት እና በኋላ ቅድመ እና ድህረ ርዕደ መሬቶች ይከሰታሉ። የመጀመሪያው ቅድመ ርዕደ መሬት ከዋናው ጋር በተመሳሳይ ቦታ የሚከሰት ቢሆንም አነስተኛ ስለሆነ ፤ ይህንን ክስተት ርዕደ መሬት መሆኑን ሊቃውንት እንኳ መናገር አይችሉም። ሌላው ድህረ ርዕደ መሬት ወይም / After shocks/ ሲሆን፤ ዋናው ርዕደ መሬት /Mainshocks/ በኋላ የሚከሰት እና በሬክተር ስኬል ሲለካ ከዋናው ያነሰ ነው። ነገር ግን ባለሙያው እንደሚሉት የበለጠ ጉዳት የሚያደርስ ነው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ድህረ ርዕደ መሬት ለሳምንታት፣ ለወራት ወይም ለዓመታት ሊቀጥል ይችላል። በቱርክ-ሶሪያ አዋሳኝ አካባቢ ከተከሰተው ርዕደ መሬት በኋላም ከ 100 ጊዜ በላይ ተከስቷል። በተለምዶ የድህረ ርዕደ መሬት መጠን ከመጀመሪያው ክስተት በአንድ ዲግሪ ያነሰ ሲሆን፤ ይህ ግን መጀመሪያው 7.8 ከተመዘገበ በኋላ የተከሰተው 7.5 ማግኒቲዩድ ያለው በመሆኑ ከተለመደው ጠንከር ያለ ነበር።

የብሪታኒያ የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ተመራማሪ ሮጀር ሙሶን እንደገለፁት አንዳንድ ጊዜ ከዋናው የሚበልጥ የድህረ ርዕደ መሬትም ሊያጋጥም ይችላል። ስለዚህ እንደ ባለሙያ፣ ምድር በምትሰጠን አዳዲስ ነገር ለመደነቅ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆን አለብን። በማለት ሳይንስ ያልደረሰባቸው እውነታዎች መኖራቸውን ገልፀው፤ ክስተቱ በምስራቅ አናቶሊያን የመሬት ንጣፍ/ፕሌት /እንደተከሰተ በተሻለ ሊገለጽ ይችላል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ዋናው ርዕደ መሬት አነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ በመባል በሶስት ሊከፈል ይችላል። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከፍተኛ የሚባለው ርዕደ መሬት በጎርጎሪያኑ 1960 ዓ.ም በደቡብ አሜሪካዊቷ ሀገር ችሊ የተከሰተው ሲሆን 9 ነጥብ 5 ሬክተር ስኬል ነበር። ሌላው በሬክተር ስኬል 9 የተመዘገበው በ2011 ዓ.ም በጃፓን የተከሰተው ርዕደ መሬት ሲሆን፤ ይህም መነሻው የባህር ዳርቻ በመሆኑ ተከታታይ ሱናሚዎችን በማስከተል በአካባቢው በሚገኝ የኒውክሌር ጣቢያ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

በቅርቡ በቱርክ እና ሶርያ የተከሰተው ደግሞ 7 ነጥብ 8 ቢሆንም የከፋ ጉዳት የታየበት ነው። ለዚህም የሕንፃዎቹ ጥንካሬ እና ችግሩ የተከሰተው ንጋት ላይ ሰዎች በመኝታ ላይ እንዳሉ መሆኑ ለጉዳቱ በምክንያትነት እየተጠቀሰ ነው። ከዚህ አንፃር ዶክተር ምንያህል ጉዳቱ ከመከሰቱ በፊትም ሆነ፤ በኋላ መደረግ አለበት የሚሏቸው የጥንቃቄ ርምጃዎች አሉ።

«እንደዚህ አይነት አካባቢዎች ላይ የከተሞች መስፋፋት እንዳይኖር ጂኦሎጅስቶች ትልቅ አስተዋጾኦ አላቸው። ከተማ ምስረታ ወይም «ሴትልመንት» ሊሆን ይችላል። ስለዚህ «ሳይቲኒክ አክቲቭ» የሆነበት ቦታ ላይ አማራጭ ካልጠፋ ለምሳሌ እንደ ጃፓን ሌላ የሚሄዱበት አኅጉር ቢኖር ደስ ይላቸዋል። ስለሌለ ግን እየኖሩ ነው። እየኖሩ ግን ርዕደ መሬትን በቴክኖሎጂ እየተቋቋሙት ነው።

እንደኛ አይነት ሀገር ብዙ ቦታ ባለበት አዳዲስ ከተማዎች መስፋፋት «ሴትልመንት» የሕንጻ ኮንስትራክሽን ያሉበት ቦታ ከሆነ ጂኦሎጅስቶች ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል። ቢያንስ ከተሰራም ጠንካራ ሕንጻ ቢሆንና በዙ «ሴትልመንት» ባይኖር ይመከራል። ስለዚህ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ዞሮ ዞሮ በቦታው እየኖሩ ከሆነ፤ መረጃ ማግኘት እና ርዕደ መሬት ከመከሰቱ በፊት ቦታውን መልቀቅ አስፈላጊ መሆኑን”ይመክራሉ።

**ሻሎም ! አሜን።**

# ዓለም አቀፍ

## ከኖቤል ሽልማቶች ጀርባ ያለው አልፍሬድ ኖቤል


በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቂያ ላይ አሜሪካ በጃፓኖቹ ሂሮሺማ እና ናጋሳኪ ከተሞች ላይ ከፈጸመችው የአውቶሚክ ቦምብ ጥቃት በተረፉት ሰዎች የተቋቋመው ኒሆን ሂዳንኪዮ የተባለው ቡድን የዘንድሮው የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል።

በአውሮፓውያኑ 1945 ከተፈጸመው አሰቃቂው ጥቃት 10 ዓመታት በኋላ የተመሠረተው ይህ ቡድን የኑክሌር ጦር መሣሪያዎች ከዓለም እንዲወገዱ በሚያደርገው ጥረት ነው በኖርዌይ የኖቤል ኮሚቴ የሰላም ሽልማት አሸናፊ የሆነው። በዓለም እጅግ የተከበረው የኖቤል ሽልማት በተለያዩ መስኮች በየዓመቱ በሥራቸው ለተመረጡ ግለሰቦች እና ቡድኖች የሚሰጥ ሲሆን፣ የኖቤል የሰላም ሽልማትም የዚህ አካል ነው።

ለዚህ ሽልማት መጀመር ምክንያት የሆነው ስዊድናዊው የንግድ ባለቤት ኢንጂነር አልፍሬድ ኖቤል ነው። ግለሰቡ ሀብቱን ለዚሁ ሽልማት እንዲሆን አበርክቷል። ግለሰቡ ዝና እና ሐብት ያገኘው ድማሚት የሚባለውን ከባድ ፈንጂ በመፍጠር ነው።

በዚህም ኖቤል የግዙፍ ጦር መሣሪያ ማምረቻ ድርጅት ባለቤት ቢሆንም፣ በመጨረሻም ገንዘቡ ለዓለም ሰላም አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሰዎች በሽልማት እንዲሰጥ ወስኗል። እአአ በ1833 በስዊዲን መዲና ስቶክሆልም ውስጥ የተወለደው አልፍሬድ ኖቤል፣ የኢንጂነር ኢማኑኤል ኖቤል እና የአንድሪቴ አህልሴል ልጅ ነው።

አባቱ ኢማኑኤል የፈጠራ ባለቤትነት መብት ያገኘባቸው በርካታ ፈጠራዎች አሉት። አንደኛው ፈጠራው የወታደሮች ቦርሳ ነው። ቦርሳው ውሃ




ውስጥ እንደመንሳፈፊያ እና በድካም ጊዜ ደግሞ እንደትራስ ሆኖ ያገለግላል። ነገር ግን ሥራው ሳይሰምርለት ቀርቶ በ 1833 ለኪሳራ በመዳረጉ ከአራት ዓመታት በኋላ አበዳሪዎቹን ሸሽት ከስዊድን ወደ ሩሲያዋ ሴንት ፒተርስበርግ ኮበለለ።

እናቱ አንድሪቴ ቤተሰቡን ለመደገፍ በሚል አምስት ዓመታትን ስቶክሆልም በሚገኝ ግሮሰሪ ውስጥ ለመሥራት ተገደደች። አማኑኤል ኖቤል ሩሲያ ውስጥ መሥራት ጀመረ። ለሩሲያ ጦር መሣሪያ ለማቅረብ በሴንት ፒተርስበርግ ሱቅ ከፈተ። የሩሲያ ባሕር ኃይልም የሚያዘጋጀውን የባሕር ውስጥ ቦምቦቹን እንዲጠቀም አሳምኗል። ቦምቦቹ እአአ ከ1853 እስከ 1856 በተደረገው የክሬሚያ ጦርነት ሴንት ፒተርስበርግን ከብሪታንያ የጦር መርከቦች ለመከላከል ጥቅም ላይ ውለው ነበር።

በዚህ ጊዜ ንግዱ ትርፋማ ሆነለት። እአአ በ1842 ደግሞ የተቀረውን ቤተሰቡን ወደ ሩሲያ ወሰደ። አልፍሬድ እና ወንድሞቹ ሳይንስ እና የቋንቋ ትምህርቶችን በግል አስተማሪዎች ተከታትለዋል። አልፍሬድ የኬሚስትሪ ትምህርቱን እንዲቀጥል በ1850 ወደ ፓሪስ ተላከ። ፓሪስ እያለም ናይትሮግሊሰሪንን የፈጠረውን ጣሊያናዊ ሳይንቲስት አስካኒዮ ሶብሬሮን ተዋወቀ።

ሶብሬሮ ያዘጋጀው ንጥረ ነገር በጣም የሚፈነዳ ፈሳሽ ነበር። ከባሩድ ብዙ እጥፍ የሚበልጥ ነበር። ለሙቀት ወይም ለግፊት ለውጦች ከተጋለጠ ይፈነዳል። ደህንነቱን መጠበቅ ከተቻለ በጣም ትርፋማ ሊሆን እንደሚችል አልፍሬድ ኖቤል አሰበ።

ከክሬሚያ ጦርነት ማብቃት በኋላ በሩሲያ የነበረው ንግድ ሥራው የተቀዛቀዘበት ኢማኑኤል ኖቤል እአአ በ1863 በድጋሚ ከሰረ። ከዚያም ወደ ስቶክሆልም ተመልሶ ከልጁ ከአልፍሬድ ጋር በመሆን ናይትሮግሊሰሪን ላይ ሙከራዎችን ማድረግ ጀመሩ። እአአ በ1864 ኬሚካሉን የተከመቸበት ክፍል ፈንድቶ የአልፍሬድ ወንድም የሆነውን ኤሚልን ጨምሮ ብዙ ሰዎችን ገደለ።

የስቶክሆልም ባለሥልጣናት በከተማው ወሰን ውስጥ የሚደረገውን የንጥረ ነገሩን ሙከራዎች ከለከሉ። አባት እና ልጅ ወርክሾፖቻቸውን ከስቶክሆልም ውጪ ወደምትገኘው ቪንተርቪከን አዛወሩ። እአአ በ1866 አልፍሬድ ኖቤል ናይትሮግሊሰሪንን ከአሸዋ ጋር በማዋሃድ በቀላሉ እንዳይፈነዳ ማድረግ ቻለ።

ይህም ሊጥ ስለሚመስል በተለያየ መያዣ ውስጥ ለማስገባት የሚመች ሆነ። በተቦረቦሩ ድንጋዮዎች ውስጥ ሲገቡ ደግሞ በመፈንዳት ድንጋዩን ይበታትኑት ጀመር። አዲሱን ፈንጂ “ዳይናማይት” ብሎ ሰየመው። እአአ በ1867 ደግሞ የፈጠራ ባለቤትነት መብት አገኘበት። ዳይናማይት (ድማሚት) የማዕድን ቁፋሮ፣ የድንጋይ ማውጣት፣ የመንገድ እና የባቡር ሃዲድ ግንባታ ሥራ ላይ ተፈላጊ ሆነ።

እአአ በ1898 በተካሄደው በስፔን-አሜሪካ ጦርነት ወቅት ደግሞ “ዳይናማይት” የተባለ ሽጉጥ ጥቅም ላይ ዋለ። በሕይወት ዘመኑ ወደ 355 የፈጠራ ባለቤትነት ያገኘው አልፍሬድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እያለ ትምህርት የመቀበል ችግር ካለባቸው ተማሪዎች መካከል መማሩን በኢንግሪድ ካርልበርግ የተጻፈው የኖቤል የሕይወት ታሪክ ያስረዳል።

አልፍሬድ ኖቤል እአአ በ1896 ሕይወቱ ሲያልፍ ወደ ጦር መሣሪያ ማምረቻ ድርጅትነት የተቀየረውን ቦፎርስ የተባለውን የስዊድን ብረታ ብረት ኩባንያን ጨምሮ 90 ፋብሪካዎች ከ20 በሚበልጡ የዓለም ሀገራት ነበሩት። ወንድሞቹ ሩሲያ ውስጥ በነበራቸው የነዳጅ ንግድ ላይ ኢንቨስት በማድረግም በሀብት ላይ ሀብት አፍርቷል።

ኖቤል በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሕክምና ወይም በፊዚዮሎጂ፣ በሥነ ጽሑፍ እና በሰላም ዘርፎች የሰውን ልጅ ለመርዳት ከፍተኛ ጥረት ላደረጉ ሰዎች ዓመታዊ ሽልማቶችን ለመስጠት ሀብቱን (3 ሚሊዮን ዶላር) አበርክቷል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

አራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ 001/2017 በጀት ዓመት የአራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ የተለያዩ አላቂ እና ቋሚ የስልጠና እቃዎች፣ አላቂ የቢሮ እቃዎች ፣ የደንብ ልብስ ፤የመኪና እቃዎች እና የመሳሰሉት በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት እና ማሰራት ይፈልጋል።በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች በጨረታ እንዲሳተፉ ይጋብዛል።

1. ተጫራቾች አራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ግንፍሌ ኩዊንስ ኮሌጅ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ወረዳ 7 ጥቃቅንና አነስተኛ የሚገኘው ግቢ አራዳ ማነፋክቸሪንግ ኮሌጅ የግዥ ክፍል በመገኘት ኮሌጁ የተጠቀሱትን የተለያዩ እቃዎች የግልፅ ጨረታ ለእያንዳንዱ ሰነድ የማይመለስ ብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ።

**2. ማንኛውም ተጫራች በጨረታው ስመወዳደር፡-**

2.1 በእቃው ወይም አገልግሎት አቅራቢነት በመንግስት ግዥ ኤጀንሲ የተመዘገበ መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

2.2 የንግድ ምዝገባ ፍቃድ የሚያቀርብ

2.3 የዘመኑን የንግድ ፍቃድ ያሳደሰና ማስረጃው ግልፅ የሆነና የሚነበብ ኮፒ ማቅረብ የሚችል የዘርፉ ዓይነት በግልፅ የተቀመጠ

2.4 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል

2.5 የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል።

**3. በጨረታ ስመሳተፍ በቅድሚያ**

3.1 ለሎት 1. ለሎት የስልጠና እቃዎች --------- ብር -----------10,000.00

3.2 ለሎት 2 የቢሮ እቃዎች አላቂ እና ቋሚ ------- ብር-----5000.00

3.3 ለሎት 3. የፅዳት እቃዎች------ብር--------5000.00

3.4 ለሎት 4 ደንብ ልብስ --------ብር---------5,000.00

3.5 ለሎት 5 የመኪና እቃዎች ------- ብር -------3,000,00

3.6 ለሎት 6. ህትመት ውጤቶች ------- ብር -------- 2,000,00

3.7 ለሎት 7 ለክሊኒክ እቃዎች ---------ብር -------- 3,000,00

3.8 ለሎት 8. የውሃ---------ብር ---------- 1,000,00

3.9 ለሎት 9. የካፍቴሪያ አገልግሎት አራዳ ማነፋክቸሪንግ ዋና ግቢ--- 5000

3.10 ሎት 10. የካፊቴሪያ አገልግሎት አዋሬ ካንፓስ ግቢ --ብር-- -5000

ለጨረታ ዋስትና የሚሆን በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ብቻ ማስያዝ ይኖርበታል፤ ያስያዙትም የጨረታ ዋስትና - ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ ጥቅምት  ድረስ ከማወዳደርያ ሰነዱ ጋር በማያያዝ በኮሌጁ የመንግስት ግዥ አስተዳደር ቡድን ቢሮ ቁጥር 57 ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የግልፅ ጨረታ ሳጥን ማስገባት አለባቸው።

4. ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ10 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የመወዳደርያ ሰነዱን መግዛት የሚቻል ሲሆን ጨረታው በ11ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።

5. ተጫራቾች የመወዳደርያ ዋጋቸውን ኮሌጁ ባዘጋጀው ሰነድ ላይ የአንዱን ዋጋ ቫትን ያካተተ ጠቅላላ ዋጋ የሚለውን በግልፅ ሞልቶ ኦርጅናል እና ኮፒ በሁለት ፖስታ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ይህን በግልጽ ሞልቶ ያላቀረበ ተጫራች ዋጋው ቫትን ያካተተ ነው ተብሎ ይወሰዳል።

6. ተጫራቾች አሸናፊ የሆኑበትን እቃ በራሳቸው ትራንስፖርት አውራጅ የጉልበት ሰራተኛ በመመደብ ለኮሌጁ ንብረት ግምጃ ቤት ያስረክባሉ።

7. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን እቃዎች በምርመራ ላይ በተቀመጠው ላይ መሆን አለበት።

8. ኮሌጁ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

9. አሸናፊ ድርጅቶች ጋር ከውል በፊት በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፀው የአቅርቦት መጠን ላይ የተገኘው ዋጋ ሳይቀየር እስከ 20% መጨመር ወይም መቀነስ ይቻላል።

**አድራሻ፡-** አራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ ግንፍሌ ኩዊንስ ኮሌጅ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ወረዳ ሰባት ጥቃቅንና አነስተኛ ሰርቶ ማሳያ ማእከል ግቢ ውስጥ

**ጥብቅ ማሳሰቢያ፡-** የጨረታ ሂደቱን ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ለወደፊቱ በመንግስት ግዥ ላይ እንዳይሳተፉ ታግደው ያስያዙት ዋስትና ይወረሳል።

ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ለመሳተፍ በሰነዱ ምርመራ ላይ በተጠቀሰው መሰረት: ሳምፕል ለሚያስፈልጋቸው ለሚወዳደርበት እቃ ቅድሚያ ሳምፕል ወይም ደግሞ ናሙና ጨረታ ከመከፈቱ በፊት ማቅረብ አለበት። ሳምፕሎችና ናሙናዎች ስድስት ወር ካለፉቸው  ለተቋሙ ገቢ ይሆናሉ።

በስፔስፊኬሽን ለሚጠየቁ እቃዎች በስፔስፊኬሽን መሰረት ካላመጡ ያስያዙት የውል ማስከበርያ ይወረሳል

**ስልክ ቁጥር፡- 01-11-26-18- 26 እና 01-11-11-16-28**

## አራዳ ማኑፋክቸሪንግ ኮሌጅ

# ስፖርት






## የቺካጎ ማራቶን በኀዘን የሚዘክረው ባለክብረወሰን

ብርሃን ፈይሳ

ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት ልክ በዚህ ሳምንት የቺካጎ ማራቶን እምብዛም ስሙ በርቀቱ የማይነሳ ወጣት አትሌት በቀዳሚነት ወደ መጨረሻዋ መስመር ሲገሰግስ ታየ፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ በይበልጥ የሳበው ግን የአትሌቱ ድል ሳይሆን ሩጫውን ሊያጠናቅቅ የሚችልበት ሰዓት ነበር፡፡ በርካቶች ባለማመን ስሜት ውስጥ ሆነው በአግራሞት እየተመለከቱት ነበር፡፡ ኬንያዊው አትሌት ኬልቪን ኪፕቱም የመጨረሻዋን መስመር አቋረጠ፤ ፊትለፊቱ ያገኘው የቺካጎ ማራቶን ዳይሬክተር ኬሪ ፒንኮውስኪ ላይም በደስታ ማዕበል ተውጦ ተጠመጠመበት፡፡ ውድድሩን ሲያስተላልፉ የቆዩ የዓለም መገናኛ ብዙሃንም ከዚህ ቀደም ማንም ያልፈጸመውን ይህንን ገድል በምን ሁኔታ ለአትሌቲክስ ወዳጆች እንደሚያደርሱት ግራ እስከመጋባት ደርሰው ነበር፡፡

የ23 ዓመቱ ወጣት አትሌት በእርግጥም ለዓመታት ሲጠበቅና በስፖርቱ ባለሙያዎች ክትትል ሲደረግበት የቆየውን የማራቶን የዓለም ክብረወሰን በማሻሻል በሰው ልጅ ታሪክ አዲስ ታሪክ ከፍቷል፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ አስገራሚ ያደረገው ደግሞ የርቀቱ የመጀመሪያ ግማሽ (21ኪሎ ሜትር) የተሸፈነው በ1:00:48 ሰዓት ሲሆን፤ ሁለተኛው ግማሽ (21ነጥብ195 ኪሎ ሜትር) ግን በ59



የዓለም የማራቶን ክብረወሰን ባለቤቱ ኬልቪን ኪፕቱም፤

ደቂቃ ከ47 ሰከንድ መሆኑ ነበር፡፡ ማጠናቀቂያው በግራንት ፓርክ የሆነውና በነፋሳማው የአየር ሁኔታ የተካሄደው ሩጫ የዓለም የማራቶን ክብረወሰን በሆነ 2:00:35 ሰዓት ተጠቃለለ፡፡ በርካቶች የተቃረቡት ነገር ግን በሰከንዶች ልዩነት ሊያስመዘግቡ ያልቻሉትን አዲስ ሰዓት ማራቶንን በቅርብ የጀመረ ወጣት ሊነግስበት ቻለ፡፡

በሰው ልጅ የስፖርት ተሳትፎ ታሪክ እጅግ ከባድና ታላቅ ጽናትን ከሚጠይቁ ውድድሮች መካከል አንዱ በሆነው ማራቶን ክብረወሰን ማሻሻል የተለየ ትርጉም ይሰጠዋል። ርቀቱ ለዘመናት 2 ሰዓትና ከዚያ በላይ መሮጡን ተከትሎም እንደ ኪፕቱም ልዩነት ፈጣሪ ሰዓት ማስመዝገብ ደግሞ የተለየ ብቃትን ይጠይቃል፡፡ እአአ በ2011 ኢትዮጵያዊው ጀግና አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ 2:03:59 በሆነ ሰዓት ማራቶንን በመሮጥ የክብረወሰን ባለቤት መሆኑን ተከትሎ ርቀቱን ‹‹ከ2:00 ሰዓት በታች መግባት ይቻላል ይሆን?›› የሚለው ሃሳብ መነሳቱን ታሪክ ያወሳል። በርካታ የስፖርት ሳይንስ ምሁራንን ጨምሮ የስፖርቱ ወዳጆች ምክንያታዊ መላምቶችን በመደርደርም ይሆናል ያሉትን ሃሳብ ሰነዘሩ፡፡

እአአ በ2017 ዘ ኢኮኖሚስት በጥናት ላይ ተመስርቶ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በርቀቱ እየተሻሻለ ያለው ሰዓት በአማካይ ከ8 እስከ 9 ሰከንድ ብቻ በመሆኑ፤ ማራቶንን ከ2 ሰዓት በታች ለመግባት ሌሎች አስርት ዓመታትን እንደሚጠይቅ ዘግቦ ነበር፡፡ ጉዳዩ ትኩረት እየሳበ መሄዱን ተከትሎም ናይኪን የመሰሉ ዓለም አቀፍ የስፖርት አልባሳትና ቁሳቁስ አምራቾች ጭምር ፕሮጀክት ቀርጸው ምንም እንኳን ተቀባይነት ባይኖረውም ሃሳቡን እውን ማድረግ ችለዋል፡፡ በአንጻሩ ባለሙያዎች እንደተነበዩት ሳይሆን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ምስራቅ አፍሪካሳያኑ ኢሉድ ኪፕቾጌ እና ቀነኒሳ በቀለን የመሳሰሉ አቦሸማኔዎች ብዙዎች ሳይንሳዊ መፍትሄ ለሚሹለት ለዚህ ጥረት መቋጫ ለማበጀት እጅግ ተቃርበው ነበር፡፡ ሁለቱ አንጋፋ የማራቶን ኮከቦች ለተዓምር እየተጠበቁ ሳለ ግን ያልተገመተው ወጣት ስሙን በወርቅ ቀለም በደማቁ ማጻፍ ቻለ፡፡

ይህ ከሆነ አንድ ዓመት ቢያስቆጥርም የአትሌቲክስ ቤተሰቡ ልብ ግን ዛሬም አትሌቱን በኀዘን ያስታውሰዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የጣፋጩ ታሪክ ባለቤትና በቀጣይም ስፖርቱን አንድ ርምጃ ሊያራምደው ይችላል የተባለለትን ወጣት አስደንጋጭ ህልፈት መርዶ ከወራት በኋላ መስማቱ ነበር፡፡ ሀገሩ ኬንያ ላይ መኪና ሲያሽከረክር በደረሰበት ከባድ አደጋ በአትሌቶች ሕይወት የመጨረሻዋን ጣፋጭ ድል በቅጡ ሳያጣጥም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡ ጀግናውን ጋብዞ ዳግም ሩጫውን ማድመቅ ያልቻለው አንጋፋው የቺካጎ ማራቶንም ዛሬ ሲካሄድ የውድድሩን መታሰቢያነት ለኬልቪን ኪፕቱም አድርጓል፡፡

‹‹በዚህ ዓመት ለእሱ እንሮጣለን›› የሚል መልዕክት በማህበራዊ የመገናኛ ገጹ ላይ ያሰፈረው የቺካጎ ማራቶን፤ የአትሌቱን ምስል የሩጫው ተሳታፊዎች በመሮጫ ቁጥራቸው ላይ እንደሚለጥፉም አስታውቀዋል፡፡ በአጭሩ የተቀጨው አሳዛኙ ኪፕቱም ሩጫውን እንደፈጸመ አቅፎት ደስታውን ያጋራው የቺካጎ ማራቶን ዳይሬክተሩ ፒንኮውስኪ በበኩሉ ‹‹በቺካጎ ጎዳናዎች ላይ ድሉን በዓይናችን በመመልከታችን እድለኞች ነን›› በማለት ገልጾታል፡፡


### ትግራይ ክልል

አቶ አረጋዊ አስፋው ሃይሉ የተመዘገበ ሰሌዳ ቁጥር ትግ-01-07895 ሞተር ቁጥር AZZWFG18934 ሻንሲ ቁጥር MD2A25BZ7FWG43875 ሞዴል MAXIMA ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስረጃ አቅርበዋል። ሠሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት የያዘ ሰው ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ለጽ/ቤታችን ሪፖርት ካላደረገ ለባለንብረቱ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**የሽሬ-እ/ስላሴ ከተማ የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ**
**ብቃት ማረጋገጫ ጽ/ቤት**

### ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አቶ ሙራድ አህመድ የሰሌዳ ቁጥር 3 ኦ/ሮ 02961 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ሊብሬ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በቀን 26/01/2017 አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የመኪናው ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያሳወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ሊብሬውን በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

የባለንብረቱ ስም የዲዶ ወረዳ ግብርና ሰሌዳ ቁጥር ኦሮ 04-07014 ሊብሬ ቁጥር 0154117 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቀን 23/01/2017 ዓ.ም አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**
**የጅማ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ፡- አሳልፈው አሸኔ እና በተከሳሽ፡- እየሩስ ጌታሁን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ምድብ 3ኛ የፍ/ብሔር ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልስዎን በፅሑፍ ለ06/02/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት እንዲያቀርቡ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን አውቀው እንዲያቀርቡ ታዟል።

**የአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የጉለሌ ምድብ ችሎት**

በከሣሽ አቶ ዳኛቸው ተፈሪ አውግቸው እና በተከሳሽ አቶ ይታያል መንግስቱ ሃይሌ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ገንዘቤን ይክፈሉኝ ሲሉ፤ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ መሠረት ተከሳሽ የፍ/ቤቱ መጥሪያ በአድራሻቸው ቢላክላቸውም ሊቀርቡ አልቻሉም። ስለሆነም ተከሳሽ በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ በ12/2/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ 2ኛ ፍታብሔር ችሎት ቀርበው መልስ እንዲሰጡ ሲል የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የልደታ ምድብ ፍታብሔር ችሎት አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የልደታ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ሰላማዊት አድማሱ አየለ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C16029 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር MBHCZC63S00A44630 ሞዴል CZF63S የሞተር ቁጥር K12MP-1414296 የሊብሬ ቁጥር - 394583 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 23/1/2017 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዮሀንስ ፀሀይ በላይ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A39079 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-5002627 ሞዴል GH-SCP10-AHPNK-D የሞተር ቁጥር 1SZ-0324831 የሊብሬ ቁጥር 057453 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 27/1/2017 አመልክተዋል። ሰሌዳው ወድቆ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፡ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቶ ወርቁ ደገፋ ጉርሙ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-18316 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር EE90-0049837 ሞዴል EE90 የሞተር ቁጥር 2E-1114327 የሊብሬ ቁጥር 222157 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 28/1/2017 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የየካ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኮከቤ ጌታቸው ሰይፉ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A93567 የተሽከርካሪዉ አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JT12LK1200059800 ሞዴል LXH12L RGMDXW የሞተር ቁጥር 2L-4757994 የሊብሬ ቁጥር 171025/402792 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 28/1/2017 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች፡- ክብሮም ኪዳነ ተጠሪ፡- መድሃኒ ክብሮም ኪዳነ

ተጠሪ ከ5/11/2014 ዓ.ም የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሣኔ ይሰጠኝ ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ተጠሪ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ6/2/2017 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት አዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል።

**የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የአቃቂ ም/ችሎት**

የባለንብረት ስም ለገሰ ፈይሳ ቶላ የህንፃ ሥራ ተቋራጭ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-44244 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር JTELB71J30-7069212 ሞዴል HZJ79L-TJMRS የሞተር ቁጥር 1HZ-0565981 የሊብሬ ቁጥር 416298 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 28/1/2017 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የየካ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አሊያንስ ትራንስፖርት ሰርቪስ አ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A42802 የተሽከርካሪዉ አይነት አውቶቡስ (ከ11 የበለጠ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር LJM6HCGE3GAS04560 ሞዴል SLK 6129 የሞተር ቁጥር ISLE310-3178564860 የሊብሬ ቁጥር 481682 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 29/1/2017 አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የልደታ ቅ/ጽ/ቤት**